


Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

የሞንትጎመሪ ካውንቲ
ፐብሊክ ስኩልስ
Montgomery County
Public Schools (MCPS)

# ስፕሪንግ 2023 እንደገና የመክፈት መመሪያ

ፌብሩዋሪ 1፣ 2023 ላይ የተሻሻለ



# ማውጫ


የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ ደብዳቤ ..... 3

ለሁሉም ፍትኃዊነትን ማረጋገጥ ..... 4

- የፀረዘረኝነት ሥርአት ኦዲት ..... 5
- ምላሽ የመስጠት ባህል ያለው የቤተሰብ ተሳትፎ ..... 5

የስራ ክንውኖች ሎጅስቲክስ እና ደህንነት ..... 6

የጤና አጠባበቅ እና ደህንነት ቅደምተከተል ..... 8

የሁሉም መመገቢያ ቦታዎች ተደራሽነት እና መጠባበቂያ እቅዶች ..... 10

የሚጠበቁ ነገሮች፡- ስርዓተ - ትምህርት እና ማስተማር ..... 11

ማስጠናት እና ማስተካከያ ጣልቃ ገብነቶች ..... 14

የሚጠበቁ ነገሮች፡- ልዩ ትምህርት ..... 17

የሚጠበቁ ነገሮች፡- MCPS ቨርቹወል አካደሚ ..... 19

ውጤት አያያዝ፣ በትምህርት መገኘት ተሳትፎ እና ተጠያቂነት ..... 20

- ዉጤት አያያዝ ..... 20
- ተጠያቂነት ..... 20
- ሪፖርት ማድረግና ክትትል ..... 25
- የጤናማነት/ድህንነት ቡድኖች ..... 25
- ቨርቹወል አካደሚ መከታተል/ተሣታፊ መሆን ..... 25

ለተማሪዎች፣ ለሠራተኞ፣ እና ለቤተሰብ ድጋፍ ..... 26

የማህበረሰብ ተሳትፎ እና ግንኙነት ..... 27

ቴክኖሎጂ ..... 28

ከመደበኛ ትምህርት ውጪ የሚሰጡ እንቅስቃሴዎች እና አትሌቲክስ ..... 29

2022-2023 የትምህርት ዓመት ቀን መቁጠሪያ ..... 30

2022-2023 የኢኖቬቲቭ ት/ቤት ቀን መቁጠሪያ ..... 31

ግብረመልስ ያቅርቡ ..... 32


የ2022 መኸር (Fall) የማቆያ መመሪያ በየአመቱ የሚታተም ስራ ላይ የሚውል ሰነድ ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ጤና እና የሰው አገልግሎቶች ክፍልን (DHHS) ጨምሮ በባለሙያ ድርጅቶች እና መንግስት ኤጀንሲዎች፣ በሜሪላንድ ስቴት ትምህርት ክፍል (MSDE) እና በሜሪላንድ ጤና ክፍል (MDH)፣ በየበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከል፣ እና በአሜሪካ የህፃናት ህክምና አካዳሚ መመሪያው ማሻሻያ ስለሚደረግበት ፖሊሲዎች እና አሰራሮች ላይ ለውጦች መደረጉ ይቀጥላል።

# የትምህርት ቤቶች ዋና ተቆጣጣሪ ደብዳቤ

ውድ ወላጆች፣ አሳዳጊዎች፣ ተማሪዎች እና ሰራተኞች

ስለ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ በስፕሪንግ 2023 እንደገና መክፈት ይህንን መመሪያ ሳካፍላችሁ ደስታ ይሰማኛል። ይሄ መመሪያ በዲስትሪክቱ በአካል ለትምህርት መመለስ፣ በሳምንት ለአምስት ቀናት ለሁሉም ተማሪዎች ላይ ሁሉን አቀፍ ማሻሻያን/ማዘመኛን ያቀርባል። መመሪያው ከስቴት እና ከአካባቢው የጤና ባለስልጣናት ጋር በመተባበር የተወሰነውን የዲስትሪክቱን ወቅታዊ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መመሪያ ጠቅለል አድርጎ ያቀርባል።

ይሄ መመሪያ ከሦስት ቅድሚ ትኩረት ከምሰጣቸውን ነገሮች ጋር አብሮ ይሄዳል፣ ይሄም በ 2022-2023 ትምህርት አመት ላይ ስኬታማ ጅማሬያችንን ያሳለጠልን/ያስኬደልን ነው።

- ከተማሪዎች፣ ከሰራተኞች እና ከማህበረሰብ ጋር መተማመንን መገንባት እና ማደስ፣
- የተማሪዎችን እና የሰራተኞችን የአእምሮ ጤንነት እና ጤናማነት መደገፍ፣ እና
- የዲስትሪክቱን ትኩረት ወደ ፍትሀዊ ማስተማር እና መማር መመለስ።

የላቀ ማስተማር እና መማር ለማቅረብ ስኬታማ የሆነ ምህዳርን ለመደገፍ የምንሰራው ስራ ላይ በምናደርገው እያንዳንዱ ውሳኔ ላይ እነዚህ ግቦች መንፀባረቅ አለባቸው። ይሄንን ስራ በመጠቀም፣ ተማሪዎቻችንን በትምህርት ስራቸው የላቀ ደረጃ እናደርሳለን፣ በዚህም የማህበረሰባችንን ብሩህ ወደፊት እናረጋግጣለን።

በእያንዳንዱ መማሪያ ክፍል ውስጥ አስተማሪ ኖሮ በአካል ተገኝቶ ለመማር፣ ራዕይ ያለው አስተዳደር እያንዳንዱን ት/ቤት እየመራ እና የድጋፍ ሰራተኞች ወሳኝ ሁሉን አቀፍ አገልግሎቶችን እያቀረቡ እና ለተማሪዎች እና ለማህበረሰቡ ድጋፍ እያቀረቡ ሁሉም ት/ቤቶች በሙሉ አቅም ተከፍተዋል። ትምህርት ቤቶች የተለመዱ የደወል ሰአቶችን፣ የክፍል መርሃ ግብሮችን እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ/ተጓዳኝ እንቅስቃሴዎችን እየተከተሉ ነው። በዲሴምበር 19፣ 2022 ላይ ባቀረብኩት ምክረ ሀሳብ መሰረት የስራ ማስኬጃ በጀት ሲለቀቅ፣ በምሄድበት ቦታ ሁሉ፣ ይሄ የትምህርት አመት እንዴት የተሻከ ስሜት እንደሚፈጥር እሰማለሁ -- ተማሪዎች እየተሳተፉ፣ በት/ቤት ማህበረሰባቸው ውስጥ ዳግም እየተሳተፉ፣ እና ት/ቤቱን ልክ እንደ ቤታቸው እየተቀበሉት ነው።

የኮቪድ-19 ቫይረስ አሁንም ማህበረሰባችን ላይ ተፅዕኖ እያሳደረ መሆኑን በማሰብ፣ በአካል ተገኝቶ መማሩን ስናካሂድ ሁላችንም ጠንቃቃ ሆነን መቀጠል ይኖርብናል። ሲታመሙ በቤት ውስጥ መቆየት፣ አየር እንዲዘዋወር ማድረግ/የቤት ውስጥ አየር ጥራትን ማሻሻያዎች እና መተላለፍን ለመከላከል ደረጃ ያላቸው የመቆጣጠሪያ ስትራቴጂዎች/ስልቶች አይነት መሰረታዊ የጤና ስትራቴጂዎች፣ ኮቪድን እንዲሁም ሌላ የመተንፈሻ አካላት ኢንፌክሽን/መበከልን ለመከላከል አሁንም በጣም አስፈላጊ አላቸው።

በወረርሽኙ ወቅት በተማርነው እና በጠንካራ ነውጥ ውስጥ ካካበትነው ጽናት የተነሳ ለት/ቤቶቻችን ሲስተም ታላቅ ልምድ የምናካብትበት ዕድል ገጥሞናል። ቢሆንም ግን በት/ቤቶቻችን፣ ተማሪዎቻችን እና ሰራተኞች ድጋፍ ላይ የመደበኛነት/ተገቢ የሆነ ስሜትን መልሰን መፍጠርን መቀጠል አለብን።

ተማሪዎቻችን ከፍተኛ-ጥራት ያለው ትምህርት እና ድጋፍን በዚህ የትምህርት አመት እና በቀጣዮች አመታት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ማህበረሰባችን በቡድን/በጋራ ተቀናጅቶ የሚሰራበትን "አሁን ሁሉም በአንድነት" መንፈስን አደንቃለሁ።

ከመልካም ወዳጅነት ጋር

Monifa B. McKnight, Ed.D.
ሞኒፋ ቢ. ማክኒት ዶ/ር
Superintendent of Schools
የት/ቤቶች ዋና ሀላፊ

ማሳሰቢያ፡- ከዋና ተቆጣጣሪው ሦስት ግቦች ጋር ተመሳሳይነትን ለማሳየት ሰነዱ በቀለም ኮድ ተደርጓል።

1. ከተማሪዎች፣ ከሰራተኞች እና ከማህበረሰብ ጋር መተማመንን መገንባት እና ማደስ።
2. የተማሪዎችን እና የሰራተኞችን የአእምሮ ጤንነት እና ጤናማነት መደገፍ።
3. የዲስትሪክቱን ትኩረት ወደ ፍትሀዊ ማስተማር እና መማር መመለስ።

# ለሁሉም ፍት ሀዊነትን ማረጋገጥ



የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ዋና የፍትሃዊነት መርህ በዲስትሪክቱ ዕቅድ እና ውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ተካቷል። የሚከተሉት የፍትሀዊነት ጥያቄዎች ለዲስትሪክቱ ዕቅድ ለማዘጋጀት ባደረግናቸው ጥረቶች በማስረጃነት እንደግብአት ጠቅመውናል።

## ይህ ተሞክሮ/ውሳኔ ለማን ያገለግላል ወይስ ማንን ችላ ይላል?

» በተግባር ወይም በውሳኔ የትኞቹ የዘር/ጎሳ ቡድኖች በአሁኑ ጊዜ በጣም ተጠቃሚ እና በጣም የተጎዱ ናቸው?

» ውሳኔው እነርሱን በተለየ ሁኔታ የሚነካቸው እንዴት ነው?

## በውይይቱ የማን ድምፅ ይበልጥ ተቀባይነት አለው/የጎላ ተፅእኖ ያደርጋል? ወይስ የማን ድምፅ በውይይቱ ተሰሚነት አላገኘም?

» ማን አልተገኘም እና እንዴትስ ሊሳተፉ ይችላሉ?

» የዚህ ተግባር/ውሳኔ አሠራር እንዴት ነው የተገለጸላቸው? ትርጉም ባለው መልኩ ተሳትፈዋል? እና በትክክል በእውነተኛ ተወክለዋል?

## በዚህ ውሳኔ ምክንያት ምን ዓይነት አሉታዊ ተጽዕኖዎች ወይም ያልታሰቡ ውጤቶች ሊከተሉ ይችላሉ?

» የትኞቹ የዘር/የጎሳ ቡድኖች አሉታዊ ተጽዕኖ ሊደርስባቸው ይችላል?

» አሉታዊ ተፅእኖዎችን እንዴት መከላከል እንደሚቻል እና በዘር እኩልነት እና ውጤቶች ላይ አዎንታዊ ተፅእኖዎችን ለማረጋገጥ ምን ድንጋጌዎች ይቀየራሉ ወይም ይታከላሉ?

## ቀጣይነት ያለው የመረጃ አሰባሰብ እና የውጤቶቹ ነፀብራቅ ምን ደረጃዎች አሉት?

» በዚህ ውሳኔ ውስጥ የምንጠቀምባቸው እና የማንጠቀምባቸው የመረጃ-ውሂብ ነጥቦች የትኞቹ ናቸው?

» ውጤቶች እና ጠቀሜታቸው እንዴት በሰነድ ተይዘው ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ይገለጻሉ?

## አፈፃፀሙን እየመሩ ያሉት ባለድርሻ አካላት ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ምን ያህል ስብጥር አላቸው?

» የተለያዩ ማንነቶች እና አመለካከቶች (ዘር፣ ጎሳ፣ ጾታ፣ ጾታዊ ዝንባሌ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የትምህርት ደረጃ፣ ሚና/አቋም) ተገቢ ውክልና ኖሯቸው የአሠራር ወይም የውሳኔ አፈፃፀምን እንዲያውቁት ይደረጋል?

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# ለሁሉም ፍትሀዊነትን ማረጋገጥ (ቀጣይ)

## የፀረዘረኝነት ስርአት ኦዲት




የፀረ-ዘረኝነት ስርዓት ኦዲት / Antiracist System Audit የመጨረሻ ሪፖርት በኦክቶበር 11፣ 2022 ላይ ከትምህርት ቦርዱ እና ለማህበረሰቡ ቀርቧል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ሱኩልስ (MCPS) ለተገኙት ውጤቶች/ግኝቶቹ መፍትሄ ለመስጠት ተከታታይ ቀጣይ እርምጃዎችን ፈጥሯል፣ የሚያካትተውም ለዲስትሪክት እና ለት/ቤት መሪዎች የስራ መርሀ ግብሮችን፣ ከተማሪ፣ ማህበረሰብ እና ከሰራተኛ ማህበራት ጋር ውይይቶችን፣ እና ለሁሉም የዲስትሪክት መሪዎች ግዴታ የሆነ ሙያዊ ትምህርትን ነው። ሁሉን አቀፍ የትግበራ ዕቅድ ሜይ 2023 ላይ ከቦርዱ ጋር የሚጋራ/የሚቀርብ ይሆናል። http://www.montgomeryschoolsmd.org/antiracist/

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አመራር እንዴት ፀረ-ዘረኛ መሪዎች መሆን እንደሚቻል በሙያዊ ትምህርት በመሳተፍ ለሪፖርቱ ግኝቶች መፍትሄ መስጠትን ጀምሯል። 60-አባላት ያሉት ፀረ-ዘረኝነት ድስትሪክት-አቀፍ ትግበራ ቡድን ግኝቶቹን ለመገምገም፣ መረጃዎችን ለመተንተን እና በዲስትሪክት-ደረጃ የትግበራ እርምጃዎችን ቅድሚያ ለመስጠት የተመቻቹ እና መዋቅር ያላቸው ውይይቶች ላይ ከሚሳተፉ ተማሪዎች፣ ሰራተኞች እና ቤተሰቦች ጋር በመቀናጀት እየሰራ ነው።

ቀጣይ እርምጃዎች

## ምላሽ የመስጠት ባህል ያለው የቤተሰብ ተሳትፎ

ሁሉም ርዕሰ መምህራን የትምህርት ቤት ማህበረሰቦቻቸውን ፍላጎት የሚያሟላ የቤተሰብ ተሳትፎ ዕቅዶችን ለማዘጋጀት ሪሶርሶችን እና ድጋፍ አግኝተዋል። መገልገያ-ሪሶርሶቹ የሚከተሉትን ያካትታሉ:-



- ደረጃ በደረጃ ውጤታማ የቤተሰብ ተሳትፎ እና ግንኙነትን ለማቀድ የሚያስችሉ ጥያቄዎችን፣ ሀሳቦችን እና ምሳሌዎችን የሚሰጥ የዕቅድ መመሪያ
- ለልዩ ልዩ የማህበረሰብ አባላት ግልፅ የሆነ የጽሑፍ ግንኙነት የማድረግ/የመፃፍ እገዛ
- የዳበረ ምላሽ ሰጪ በራሪ ወረቀቶችን፣ እና ለወላጅ የሚቀርብ ፓወር ፖይንቶችን ስለማዘጋጀት መሰረታዊ ፍንጮች

የማህበረሰብ ተሳትፎ ፖሊሲ / Community Engagement Policy



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# የሥራ ክንውኖች፣ ሎጂስቲክስ እና ደህንነት



## የደወል ሰአቶች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶች ለ 2022-2023 የትምህርት ዓመት የቅድመ ወረርሽኙን ጊዜ መደበኛ የደወል ሰዓታቸውን ይጠብቃሉ።

| የክፍል ደረጃ | ጊዜ | የቀናት ርዝመት |
|---|---|---|
| ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት | 7፡45 a.m.-2፡30 p.m. | 6 ሰአት 45 ደቂቃ |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት | 8:15 a.m.–3:00 p.m. | 6 ሰአት 45 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 1 | 9:00 a.m.–3:25 p.m. | 6 ሰአት 25 ደቂቃ |
| ኤለሜንታሪ ትምህርት ቤት ደረጃ (Tier) 2 | 9:25 a.m.–3:50 p.m. | 6 ሰአት 25 ደቂቃ |

## የተማሪና ሰራተኞች ደህንነት እና ጥበቃ

MCPS ለተማሪዎች እና ሰራተኞች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ምቹ የሆነ የመማሪያ አካባቢ/ምህዳር የመፍጠሪያ ሁኔታዎች ላይ ትኩረት ማድረጉን ቀጥሏል። የላቀ የአዕምሮ ጤና እና ጤናማነት ድጋፎች፣ የደህንነት እና ጥበቃ አገልግሎቶች መስፋፋቶች፣ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ አባላትን ፕሮግራምን በ2022-2023 የትምህርት ዘመን እነዚህን ሁኔታዎች ለመፍጠር በጣም አስፈላጊ ናቸው። የአዕምሮ ጤናን በተመረጡ ት/ቤቶች ለማሳደግ MCPS ከጤና ቢሮ እና ከሰው አገልግሎቶች ጋር በትብብር ይሰራል እና የማህበራዊ ሰራተኞች ሰልጥነዋል እና በእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተመድበዋል። MCPS የደህንነት እና ጥበቃ ሰራተኞችን ጨምሯል፣ ይሄም በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚገኘውን የት/ቤት ደህንነት አገልግሎት ለማሳደግ የሚዟዟሩ ጥበቃዎችን መቅጠርን ያካትታል። በተጨማሪም ይሄ የማህበረሰብ ተሳትፎ አባላት ፕሮግራምን በሙሉ አመት የሚተገበርበት ይሆናል፣ የተዘጋጀውም ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ ቢሮ ጋር በአጋርነት እና ከበርካታ የማህበረሰብ ባለድርሻ አካላት ቡድኖች ጋር በትብብር ሲሆን፣ አላማውም ተማሪዎች ለማህበራዊ-ስሜታዊ እና የጤና ድጋፎች ያላቸውን ፍላጎቶች እያዳረሱ የደህንነት አገልግሎቶችን ለማቅረብ ነው።

## ተማሪዎችን ደህንነታቸው በተጠበቀ ሁኔታ የማጓጓዝ አገልግሎት

በ 2022-2023 የትምህርት ዓመት፣ በቅድመ ወረርሽኝ በነበረው መደበኛ የመጓጓዣ መስመሮች ይቀጥላል። ቤተሰቦች ለተመደበላቸው ትምህርት ቤት የአውቶቡስ መስመሮችን እንዲያውቁ ተደርጓል። በተጨማሪም ይሄን መረጃ ማግኘት የሚቻለው በMCPS ድህረገፅ montgomeryschoolsmd.org/schools/ ነው። ከዝርዝሩ (menu) መካከል ት/ቤቱን ይምረጡ እና ለት/ቤቱ የተቀመጠውን የባስ መንገዶች/መስመሮች ሰነድ አግኙ።

ተማሪዎች በትምህርት ቤት አውቶቡሶች ላይ የፊት መሸፈኛ ጭምብል ማድረግ አይጠበቅባቸውም ነገር ግን ወረርሽኙ በማህበረሰብ ውስጥ በሚያስከትለው የስርጭት ደረጃዎች እና በህዝብ ጤና ጥበቃ ባለስልጣናት መመሪያ ላይ ተመስርቶ ይህ ሊለወጥ ይችላል።

የአውቶቡስ ሹፌሮች በየቀኑ የአውቶቡሶችን ንፅሕና ይጠብቃሉ እና በጀርም መከላከያ ያጸዳሉ። የአየር ሁኔታ እና ሌሎች የደህንነት ጉዳዮችን ታሳቢ በማድረግ ለመተግበር አመቺ በሚሆንበት ጊዜ፣ የባስ ሹፌሮች ንፅህ አየር የተሻለ እንዲዟዟር እና በሽታው የሚተላለፍበትን ሁኔታ ለመቀነስ መስኮቶችን ሁሌም ክፍት ያደርጋሉ።

በየቀኑ ከጉዞ በፊት የአውቶቡሶች ደህንነት ፍተሻ ሲደረግ፣ የአውቶቡስ ሹፌሮች እና የአውቶቡስ ረዳቶች የኮቪድ-19 መከላከያ ተጨማሪ ጭምብሎች፣ የእጅ ማጽጃ እና የጽዳት/የፀረ-ተዋስ አቅርቦቶች መኖራቸውን ያረጋግጣሉ። የአውቶቡስ ሾፌሮች እና የአውቶቡስ ረዳቶች ወቅታዊ የኮቪድ-19 መከላከል ጥንቃቄ በሚመለከት በየቀኑ የደህንነት ፕሮቶኮሎችን በሥራ ላይ ስልጠና ወቅት፣ በሬድዮ ማስታወቂያ ምልልሶች፣በጋዜጦች እና በቀጥታ ከሱፐርቫይዘሮች ስልጠና መውሰዳቸው ይቀጥላል።

ብዙ ወላጆች ተማሪዎቻቸውን ወደ ት/ቤት ሲያደርሱ እና ከት/ቤት ሲወስዱ በአንዳንድ ሁኔታዎች ትምህርት ቤቶች ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ ጋር በጥምረት ለማስተናገድ እየሰሩ ነው። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ወደ ት/ቤት መሄጃ አስተማማኝ መስመሮች ፕሮግራም ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት ማድረስ እና ከት/ቤት ስለማምጣት ለቤተሰቦች ሌላ አማራጭ ለማቅረብ የትምህርት ቤት ጉዞ አውቶቡሶች እንዲፈጠሩ እያበረታታ ነው።




Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# የምግብ እና አልሚ ምግብ አገልግሎቶች



የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ሱኩልስ (MCPS) የምግብ እና የአልሚ ምግብ አገልግሎቶች ክፍል (DFNS) በ 2022-2023 የትምህርት ዘመን ላይ መደበኛ የምግብ አገልግሎቶቹን ቀጥሏል።

## ለማስታወስ የሚያስፈልግ

በሜሪላንድ ውስጥ ለቅናሽ ዋጋ ምግብ ብቁ የሆኑ ተማሪዎች ከዚህ አመት ጀምሮ ለቁርስ ወይም ለምሳ ምግብ አይ ከፍሉም።

## ቁርስ

መደበኛ ዋጋ $1.30;
የቀነሰ ዋጋ ክፍያ የለውም

## ምሳ

መደበኛ ዋጋ $2.55 (አንደኛ ደረጃ)፤
$2.80 (መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ)፤
በሁሉም ደረጃዎች የቀነሰ ዋጋ፡- ክፍያ የለውም

ከዚህ አመት ጀምሮ፣ FARMS ፎርሞችን ወደመጠቀም ስለምንመለስ ተማሪዎች በካርዱ ላይ ያለውን ባር ኮድ ስካን እንዲያደርጉ ወይም የምሳ አካውንታቸውን ለማየት ፒን ቁጥራቸውን እንዲያስገቡ እንጠይቃለን። ከልዩ ፒን ቁጥር ይልቅ፣ ተማሪዎች የተማሪ መታወቂያ ቁጥራቸውን ይጠቀማሉ። የተማሪ መታወቂያ ቁጥር ተማሪዎች Chromebook ለመክፈት የሚያስገቡት ቁጥር ነው።

የነጻ እና የቅናሽ ዋጋ የምግብ ሲስተም (FARMS) የብቁነት መረጃ እና የመተግበሪያ ሂደት፡- FAARMS ማመልከቻው ተሻሽሏል። ፍላጎት ያላቸው ቤተሰቦች በየትምህርት ዓመቱ እንደገና ማመልከት አለባቸው። ኦንላይን/በይነመረብ ማመልከት ተመራጭ የማመልከቻ ዘዴ ስለሆነ ቤተሰቦች www.MySchoolApps.com ላይ እንዲያመለክቱ አጥብቀው ማበረታታት አለባቸው። ቤተሰቦች አሁን ማመልከት ይችላሉ።

# የጤና አጠባበቅ እና ደህንነት



ለ 2022-2023 የትምህርት ዓመት ተማሪዎች እና ሰራተኞች ወደ ትምህርት ቤት ሲመለሱ፣ MCPS አስተማማኝ እና በፍትሃዊነት በአካል ለማስተማር፣ እንዲሁም የተማሪዎችን እና የሰራተኞችን አካላዊ እና አእምሯዊ ጤንነት እና ደህንነት ቅድሚያ ለመስጠት ቁርጠኛ ነው። የቁጥጥር መስፈርቶች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ጤና ቢሮ እና የሰው አገልግሎቶች (DHHS) መመሪያ፣ የሜሪላንድ ስቴት ትምህርት ክፍል (MSDE) እና የሜሪላንድ ጤና ቢሮ (MDH)፣ የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከሎች እና የየአሜሪካ የህፃናት ህክምና አካዳሚ የMCPS ደግሞ የመክፈት ዕቅድ ጥረቶች ላይ አሁንም ግብዓት ሆነው ቀጥለዋል።

MCPS በማህበረሰቡ ውስጥ የወረርሽኙን ስርጭት እና የአካባቢ ስጋት ሁኔታዎች ላይ በመመስረት ከተወሰኑ የኮቪድ-19 መከላከያ ስልቶች በተጨማሪ በሽታን ለመከላከል የእለት ተእለት የጤና ጥበቃ ስልቶችን ያካተተ ባለ ብዙ ሽፋን የጤና እና የደህንነት ፕሮቶኮል መተግበሩን ይቀጥላል። በተለይም፣ MCPS የሚከተሉትን የጤና እና የደህንነት ትግበራዎች በት/ቤቶች እና ቢሮዎች ላይ ተግባራዊ ያደርጋል።

## ዋና የጤና አጠባበቅ ስልቶች

በህመም ጊዜ ቤት ውስጥ መቆየት፣ እጅ መታጠብ፣ እና በሚያስሉበት ወይም በሚያስነጥሱበት ጊዜ አፍን መሸፈንን ጨምሮ መሰረታዊ የጤና አጠባበቅ ክንውኖች በትምህርት ቤቶች ውስጥ የበሽታ መስፋፋትን ለመከላከል ወሳኝ መሳሪያዎች ሆነው ይቀጥላሉ። ተጨማሪ ዋና የጤና አጠባበቅ ስልቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

### ጽዳት

የሰለጠኑ የህንጻ አገልግሎት ሰራተኞች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) መገልገያዎች ውስጥ ከፍተኛ/ተደጋጋሚ ንክኪ ያላቸውን ቦታዎች በሙሉ አዘውትረው ማፅዳታቸውን እና ከብክለት መከላከላቸውን ይቀጥላሉ። ለበር እጀታዎች፣ የመብራት ቁልፎች፣ የእቃ ማጠቢያ መያዣዎች፣ እና ሌሎች በተደጋጋሚ ለሚነካኩ ነገሮች ልዩ ትኩረት ይሰጣል። በጋራ ቦታዎች ያሉ መጸዳጃ ቤቶች በቀን ውስጥ በተደጋጋሚ ይጠረጋሉ እና በፀረ-ተዋስ ይጸዳሉ። ከጀርም የሚያጸዱ ኬሚካሎች በሠራተኞች አማካይነት ጥቅም ላይ የሚውሉ ሲሆን፣ ለፀረ-ተዋህስያን ማጥፊያ መጥረጊያዎችን ወይም ሌሎች ኬሚካሎችን በሚጠቀሙበት ጊዜ ተማሪዎች ለመርዳት/ለማገዝ አይሳተፉም። ሰራተኞች ተገቢ ማጽጃዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፣ ነገር ግን በየቤቱ የሚመረቱ ምርቶች በ MCPS ህንፃዎች ውስጥ በጥቅም ላይ አይውሉም።


### ክትባት

MCPS ብቁ የሆኑ ተማሪዎች እና ሰራተኞች ሲዲሲ (CDC) ከተላላፊ በሽታዎች ለመጠበቅ የሚመክራቸው ክትባቶች ላይ በየጊዜው እየተከታተሉ እንዲያውቁ ትኩረት ሰጥቶ ይመክራል። MCPS ከ DHHS ጋር በመተባበር፣ በትምህርት ቤቶች እና በማህበረሰቡ ውስጥ ተደጋጋሚ እና ነፃ የክትባት ክሊኒኮችን በመክፈት፣ በተጎዱ ማህበረሰቦች እና Title I ትምህርት ቤቶች ላይ በማተኮር ተጨማሪ የኮቪድ-19 ክትባቶችን እና ቡስተሮችን ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች እና ቤተሰቦች ሰጥቷል። አሁን ላይ MCPS ሰራተኞች የኮቪድ-19 ክትባት ወይም በህክምና ነፃ የመሆን ማረጋገጫ ዶክመንት እንዲያቀርቡ ይጠይቃል።

### የአየር ማናፈሻ እና የቤት ውስጥ አየር ጥራት

MCPS የአየር ዝውውርን ለማሻሻል እና የተማሪዎችን እና የሰራተኞችን ጤንነት እና ደህንነት ለማረጋገጥ የሚከተሉትን እርምጃዎች ወስዷል፦

1. ሁሉም ነባር ሲስተሞች እና መሳሪያዎች ተፈትሸዋል።
2. ከፍተኛውን የተሻሻለ የአየር ማጣሪያ (MERV) ለመጠቀም እንዲያስችል ሁሉንም HVAC ማጣሪያዎች ለመተካት መርሐግብር ተዘጋጅቷል።
3. በህንፃዎች ውስጥ ንጹህ አየር ማናፈሻ መጨመር።
4. ተለይተው በታወቁ ክፍሎች፣ ቢሮዎች እና የጤና አገልግሎት በሚሰጥባቸው ቦታዎች ለመጠቀም ተንቀሳቃሽ የአየር ማጽጃዎች ተገዝተዋል።
5. የተሻሻለ HVAC ሲስተም ስራ ክፍሎቹ ከመያዛቸው በፊት እና በኋላ በህንፃዎች ውስጥ ያለው አየር "እንዲፀዳ" የሚያስችል የተራዘመ የአገልግሎት ጊዜ አለው።




### የእጅ ጀርም ማጽዳት እና እጅ መታጠብ

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ሕንፃዎች ውስጥ በሚገኙበት ጊዜ አዘውትረው እጃቸውን እንዲታጠቡ ይበረታታሉ። የእጅ ማጽጃ ለተማሪዎች እና ለሰራተኞች ይሰጣል፣ በህንፃዎች ውስጥ የንፅህና መጠበቂያ ጣቢያዎች ይኖራሉ።

# ጤንነት እና ደህንነት (ቀጣይ.)



## የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ቅነሳ

CDC የሚያስተላልፈውን በማህበረሰብ ውስጥ የበሽታ ስርጭት ደረጃዎች መረጃ እና በአካባቢው ከፍተኛ ተጋላጭነት ባላቸው ሁኔታዎች ላይ በመመስረት በትምህርት ቤቶች ውስጥ የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመከላከል ተጨማሪ ተደራራቢ ስልቶች ተግባራዊ ይደረጋሉ። ተጨማሪ የኮቪድ-19 ስርጭት መከላከያ ስልቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

### የኮቪድ -19 ምርመራ ተደራሽነት

አሁን ላይ ሲዲሲ (CDC) በየጊዜው የሚደረግ የመለያ ምርመራ ከመዋለ ህፃናት-12 (K-12) ት/ቤቶች ላይ እንዲደረግ አይመክርም። ከፍተኛ አደጋ ተጋላጭ ሁኔታዎች ላይ MCPS የመለያ ምርመራን ጥቅም ላይ ያውላል እና ይደግፋል፤ ይሄም የሚያካትተው ት/ቤት መሰረት ያደረገ ወረርሽኝ እና ከከፍተኛ-ስጋት ተግባራት ጋር ተዛማጅ በሆኑ ስልታዊ ጊዜያት፤ ትላልቅ መሰባሰቦች ወይም የት/ቤት እረፍት ተከትሎ ከፍተኛ ጉዞ የሚኖርበትን ጊዜ ነው። ከሞንትጎመሪ ካውንቲ DHHS የት/ቤት ጤና አገልግሎቶች (Montgomery County DHHS School Health Services) ጋር በመተባበር፣ MCPS በትምህርት ቀን ላይ የኮቪድ-19 ምልክቶችን የሚያሳዩ ተማሪዎችን መመርመርን መደገፍ ይቀጥላል። ደህንነቱ የተጠበቀ በአካል ተገኝቶ መማርን ለመደገፍ መሰረታዊ ስትራቴጂ ኮቪድ-19 የለባቸውን ሰዎች መመርመር እና መለየት ስለሆነ፣ MCPS ለምርመራ ፍትሀዊ ተደራሽነትን መደገፉን ይቀጥላል፤ እና ሰራተኞች እና ተማሪዎች የምርመራ ውጤታቸው ኮቪድ እንዳለባቸው ሲያሳይ በMCPS ሪፖርት መተግበሪያ ላይ ራሳቸው-ሪፖርት እንዲያደርጉ በጣም ያበረታታል።

### ፊት መሸፈን

በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቦርድ መሠረት፣ በሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ ውስጥ ማስክ/ጭምብል መጠቀም ግዴታ አይደለም፤ እና የየአካባቢ ትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች ደህንነትን ለመጠበቅና በአካል-ተገኝቶ መማርን ለማስቀጠል ጭምብልን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ሊወስኑ ይችላሉ። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ሱኩልስ (MCPS) በበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከሎች የኮቪድ-19 የመነጠል እና የመወሸብ/ኳረንቲን መመሪያዎች መሰረት ጭምብሎች መደረጋቸው ቀጥሏል፤ እንዲሁም በጤና እንክብካቤ ቦታዎች ውስጥ (የት/ቤት ጤና ክፍሎችን ጨምሮ)፣ በአካባቢ ጤና ክፍል መመሪያ መሰረት ነው። ጭምብሎች ለሁሉም ሰራተኞች እና ተማሪዎች ይዘጋጃሉ፤ በማንኛውም የኮቪድ-19 ወረርሽኝ የማህበረሰብ ስጋት ደረጃ ላይ ጭምብል መጠቀም የሚመርጡ ግለሰቦች ይደገፋሉ። በአካባቢያዊ ወረርሽኞች፣ ከፍተኛ ስጋት ባለባቸው ሁኔታዎች፣ ወይም በይበልጥ፣ የኮቪድ-19 ስርጭት በማህበረሰብ ውስጥ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ ጭንብል ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል።

### ከንክኪ ነፃ የሆኑ ክፍሎች

ለ2022-2023 የትምህርት ዘመን፣ ት/ቤቶች የመለያ/ለብቻ ማቆያ እና የህክምና ድጋፎች መስጫ ክፍሎችን ለይተው ስራ ላይ አያውሉም። በምትኩ፣ MCPS በትምህርት ቀን ኮቪድ-19 ምርመራ እንዳለባቸው የሚያሳይ ተማሪዎች በአፋጣኝ እስኪወሰዱ ድረስ በመጠባበቅ ላይ እያሉ ጭንብል እንዲያደርጉ እና ከሌሎች በአካል እንዲርቁ ያደርጋል።

### አካላዊ ርቀት

MCPS ወደ ቅድመ-ወረርሽኝ የመማሪያ ክፍል አቅምና እና የቦታ አጠቃቀም ይመለሳል። CDC የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች አካላዊ ርቀትን በተቻለ መጠን እንዲተገብሩ የሚያበረታታ ቢሆንም፣ ተማሪዎችን በአካል ከመማር እንዲገለሉ የሚያደርግ የርቀት መስፈርቶችን ከመተግበር ያስጠነቅቃል። ት/ቤቶች ለምሳ እና ማስክ ሳያደርጉ ለሚካሄድ ትምህርታዊ እና ማህበራዊ ተሞክሮዎች ለተማሪዎች ከክፍል ውጪ ያሉ ቦታዎችን የሚቻል ሲሆን ይጠቀማሉ።

### የንክኪ መነሻን ማግኘት እና በሽታውን ስለ ማሳወቅ

[የተሻሻለውን MSDE/MDH መመሪያ](#) መሠረት በማድረግ፣ MCPS ከአሁን በኋላ በኮቪድ-19 ለተያዙ ግለሰቦች የንክኪ ግንኙነት ፍለጋ አያደርግም። በከፍተኛ-አደጋ ምድብ ሁኔታ ወይም በአካባቢው ወረርሽኝ የኮቪድ-19 ተጠቂ ከተገኘ ሰራተኞች እና ቤተሰቦች የተጋላጭነት ማሳወቂያ ይደርሳቸዋል። በከተማ እና በአካባቢው የወረርሽኝ-ተጓዳኝ በት/ቤቶች የኮቪድ-19 ጉዳዮች ላይ በአሉት ደንቦች መሰረት MCPS ከሰው አገልግሎቶች ክፍል (DHHS) ጋር በመተባበር የወረርሽኝ ምርመራን ይደግፋል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ሱኩልስ (MCPS) ሪፖርት የተደረጉ የኮቪድ-19 ግኝቶችን/ጉዳዮችን መረጃዎች ለእኛ ሰራተኞች፣ ተማሪዎች እና ማህበረሰብ በኮቪድ-19 ሰሌዳችን (dashboard) ላይ ተደራሽ ማድረጉን ቀጥሏል። ይሄ ሰሌዳ (dashboard) ሪፖርት በሚደረጉ ግኝቶች/ጉዳዮች መሰረት በየቀኑ ማሻሻያ ይደረግበታል እና የሚያሳየውም ግኝቶችን/ጉዳዮችን በሁለቱም ማለትም በእያንዳንዱ ት/ቤት እና ቢሮ ደረጃ እንዲሁም ለት/ቤት አመቱ ስርዓት አቀፍ መረጃዎችን ነው።

### ለብቻ ተገልሎ መቆየት (ኳራንቲን)

[በሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከሎች (CDC) እና ሜሪላንድ ስቴት ትምህርት ክፍል (MSDE)/ሜሪላንድ ጤና ክፍል (MDH) የተሻሻለ መመሪያ](#) መሰረት፣ የክትባት ደረጃ ምንም ሆነ ምን፣ ከአንዳንድ ከፍተኛ-ተጋላጭነት የመሰባሰብ ቦታዎች ውጪ ለኮቪድ-19 ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች ከአሁን በኋላ ውሸባ/ኳረንቲን የሚመከር አይደለም። ኮቪድ-19 ከተገኘባቸው ግለሰቦች ጋር የቅርብ ግንኙነት እንዳላቸው የተለዩ ተማሪዎች የበሽታ ምልክት እስካልታየባቸው ድረስ እና ማስክ የማድረግ፣ የምርመራ እና ከቅርብ ግንኙነት ተጋላጭነት በኋላ ምልክቶች ለሚያሳዩ ግለሰቦች የወጡትን መመሪያዎች እስከተሉ ድረስ በአካል ተገኝተው መማር ይችላሉ። ተማሪዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ጭምብል በማያደርጉባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ተጨማሪ ተግባራት ሊመከሩ ይችላሉ። የምርመራ ውጤታቸው ኮቪድ-19 እንዳለባቸው የሚያሳይ ሰራተኞች እና ተማሪዎች የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከሎች (CDC) መነጠል/ለብቻ መሆን እና ጭምብል ማድረግ ላይ ያወጣቸውን መመሪያዎች እንዲከተሉ ይመከራሉ።

# የሁሉም መመገቢያ ቦታዎች ተደራሽ ነት እና መጠባበቂያ ዕቅዶች

## ወደ ሁሉም የመመገቢያ ቦታዎች ተደራሽነት

ተማሪዎች በካፍቴሪያዎች እና በሌሎች የመመገቢያ ቦታዎች ቁርስ እና ምሳ መብላት ይችላሉ። ተማሪዎች ለቫይረሱ ስርጭት ተጋላጭ እንዳይሆኑ ከቤት ውጭ በሆኑ ገላጣ አካባቢዎች እንዲመገቡና ትምህርት ቤቶች በተቻለ መጠን ከቤት ውጭ የሚገኙ ክፍት ቦታዎችን እንዲጠቀሙ እናበረታታለን። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ገላጣ ክፍት ቦታዎችን/ካምፓስ ለምሳ ወደመጠቀም ሊመለሱ ይችላሉ።

## መጠባበቂያ ዕቅዶች

ዋናው ቅድሚያ የሚሰጠው በሳምንት ለአምስት ቀናት በአካል ተገኝቶ ማስተማር ቢሆንም፣ MCPS በትምህርት አመቱ ሊነሱ የሚችሉ ከኮቪድ-19 ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለመፍታት ቀጣይነት ያለው የመጠባበቂያ እቅድ በማዘጋጀት ላይ ይገኛል።

የምርመራ ውጤታቸው ኮቪድ-19 እንዳለበት/ባት የሚያሳይ ተማሪ በህመም ምክንያት መነጠል ወይም ት/ቤት መቅረት ከፈለገ/ች፣ MCPS በዚህ ወቅት ላይ የተማሪ መማር ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ መቋረጦችን ለመቀነስ ይጥራል።

ፍቃድ በአለው የካውንቲ ወይም የስቴት/ክልል መንግስት ኤጀንሲ በኩል እንዲዘጉ ካልታዘዙ በስተቀር የትምህርት ቦርዱ የት/ቤት ህንፃዎችን አይዘጋም እና ሙሉ በሙሉ ወደ ቨርቹዋል ትምህርት አይቀይርም። አመራሮች የት/ቤት ህንፃዎች ላይ ቁጥር እንዲቀነስ ከአዘዙ፣ የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ቀኑን ሙሉ የመምጣት እድል ይሰጣቸዋል። ግብዓቶች በካንቫስ (Canvas) በኩል ይላካሉ። በሁለተኛ ደረጃ፣ ተማሪዎች ከክፍል ትምህርት ጋር የተገናዘቡ ተግባራትን በካንቫስ መድረክ ያገኛሉ። ከትምህርት አይነት አስተማሪዎች ጋር የመመዝገብ እድሎች ቀኑን ሙሉ ይሰጣሉ።

ከበርካታ ምክንያቶች ግምገማ በኋላ፣ ለአጠቃላይ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ጤና እና ደህንነት ፍላጎት ሲባል አንድ ትምህርት ቤት ለአምስት ቀናት ወደ ቨርቹወል ትምህርት ሊዛወር ይችላል። በአካል የሚሰጠውን ትምህርት ለአፍታ ለማቆም ውሳኔ የሚሰጠው በርካታ ቁልፍ ነገሮችን በመገምገም ሲሆን:- እነዚህ ቁልፍ ነገሮች እያንዳንዱን ፕሮግራሞች እስከ ተግባራዊ ዝግጁነት ያሉትን ሁኔታዎች እያንዳንዱ ትምህርት ቤት የሚገኝበት ልዩ ሁኔታ ግምት ውስጥ ገብቶ ነው። የተናጠል ትምህርት ቤት ማህበረሰቦች የተደረገውን ለውጥ እና ለዚያ ትምህርት ቤት ውሳኔ ለማሳወቅ አስፈላጊ የሆነበትን ምክንያት ዝርዝር የሚገልጽ ደብዳቤ ይደርሳቸዋል።

ወደዚህ ውሳኔ ለመድረስ ዋነኞቹ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው:-

» የተማሪዎች ት/ቤት የመገኘት ሁኔታ (በአማካይ ሶስት ቀን ብቻ ሆኖ ሲገኝ)

» የሰራተኞች ከሥራ የመቅረት ሁኔታ (በአማካይ ከሶስት ቀን ያልበለጠ ሲሆን)

» በጠዋት እና ከሰአት በኋላ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የአውቶቡስ መስመሮች ብዛት (በአማካይ ሶስት ቀን ከሆነ)

» በቅድሚያ ያልቀረቡ የተተኪ ጥያቄዎች ብዛት (በአማካይ የሶስት ቀን እየታየ)

» ባለፉት 10 ቀናት ውስጥ በተማሪዎች እና በሰራተኞች ላይ የተከሰቱ የ COVID-19 ሁኔታዎች

» ከትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ብዙ ባለድርሻ አካላት የተሰጠ ምክረሃሳብ

ለዚህ የአሠራር ለውጥ ለመዘጋጀት መምህራን ተማሪዎችን በርቀት ትምህርት የሚያሳትፉበት አንድ ቀን የዝግጅት ጊዜ ይኖራቸዋል። ከዚያ ቀጥሎ ሙሉ በሙሉ በአስተማሪ የሚመራ የቨርቹወል ትምህርት ይሰጣል። ቤተሰቦች በቨርቹወል ትምህርት ጊዜ ስለሚጠበቁ ነገሮች መረጃ፣ መመሪያ እና ሪሶርሶችን ያገኛሉ። የሕጻናት እንክብካቤ መርሃ ግብሮች በታቀደው መሰረት ሊቀጥሉ ይችላሉ።

የአደጋ ጊዜ የማስተማሪያ ዕቅዶች የሚፈጠሩት በካውንቲው ወይም ክልሉ/ካውንቲ በአሉት የጤና ሁኔታዎች የተነሳ ፍቃድ በአለው የካውንቲ ወይም የስቴት መንግስት ኤጀንሲ በኩል የት/ቤት ህንፃዎች ላይ ቁጥር እንዲቀነስ ከአዘዙ ብቻ ነው።

# የሚጠበቁ ነገሮች፡- ሥርዓተ -ትምህርት እና ማስተማር



## ለስኬታማ ማስተማር ማቀድ

የ MCPS ዋና ዓላማ ሁሉም ተማሪዎች በወደፊት ሕይወታቸው እንዲበለጽጉ የሚያግዝ ጠንካራ የትምህርት ፕሮግራም መስጠት ነው። 2022-2023 የትምህርት ዓመት፣ MCPS የትምህርት መቆራረጥን ለማቃለል ሲባል የድጋፍ ዕቅዶችን በመተግበር ሁሉም ተማሪዎች ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲሰሩ ያደርጋል። ዲስትሪክቱ ሁሉም ተማሪዎች ተደራሽነት እንዲኖራቸው እና ማንኛውም በወረርሽኙ ምክንያት የተስተጓጎለባቸውን ትምህርት ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ የብዙ ዓመት ዕቅዶችን አዘጋጅቷል። መመሪያ፣ ድጋፍና የሙያ ትምህርት መምህራን ተማሪዎች ያመለጧቸውን ትምህርቶች ወይም በጣም ባጠረ ሁኔታ የተማሩት ትምህርት ላይ በማተኮር ጠንካራ መሠረት እንዲገነቡ ያስችላቸዋል። መምህራን የማስተማር እቅድ በሚያወጡበት ጊዜ፣ ከቅድመ መዋእለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል የሜሪላንድ የኮሌጅ እና የሙያ ዝግጁነት ደረጃዎችን (MCCRS) የጠበቀ እና ከስቴት ደረጃዎች ጋር በማጣጣም ዋና የተማሪ ፍላጎቶችን በማሟላት ላይ የሚያተኩር ነው።

በአንደኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች  የማስጠናት ጣልቃ ገብ ድጋፍ የሚሰጥባቸው ጊዜያት በትምህርት መርሃ ግብሮች ውስጥ ተካቷል። በተጨማሪም፣ በትምህርት ላይ ጉልህ ክፍተቶችን የሚያሳዩ ተማሪዎች ከመደበኛ ትምህርት በኋላ በሚሰጥ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ለመሳተፍ ወይም ከውጭ አጋሮች ድጋፍ የማግኘት ዕድል ይኖራቸዋል።

### ሒሳብ ማሻሻያ ዕቅድ

የ MCPS የሂሳብ ፕሮግራም በሁሉም ደረጃዎች ያሉ ተማሪዎችን ጠንክረው እንዲሠሩ እንዲገዳደር የተቀየሰ ነው። ግቡ ተማሪዎች እንደአስፈላጊነቱ አልጀብራ 1 በ 7ኛ፣ 8ኛ ወይም 9ኛ ክፍል በተሳካ ሁኔታ እንዲያጠናቅቁ እና የላቀ ደረጃ ምደባ (AP) እና International Baccalaureate (IB) ትምህርቶችን ጨምሮ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ለከፍተኛ ደረጃ የሂሳብ ትምህርት መዘጋጀት ነው። በወረርሽኙ ምክንያት የተስተጓጎሉ/ያመለጧቸውን ትምህርቶች ለማካካስ በእቅዱ ላይ ማስተካከያዎች እየተደረጉ ነው። የሂሳብ ማገገሚያ ዕቅድ መመሪያ መርሆዎች ምንድናቸው?

- በየሳምንቱ አምስት ቀናት የሂሳብ ትምህርት ይሰጣል።
- ተማሪዎች ያሉበትን የክፍል ደረጃ በሚመጥን ትምህርት ላይ ይሳተፋሉ።
- መማር በትምህርቱ ዋና ሥራ ላይ እና የኋላ ድጋፍ/ተጨማሪ ሥራዎች ላይ ያተኩራል።

እቅዱን ለማየት፣ እባክዎእዚህ ክሊክ ያድርጉ።

### የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ የማንበብና መፃፍ ማሻሻያ እቅዶች

» የመጀመሪያ ደረጃ ELA እቅድ

» የሁለተኛ ደረጃ ELA እቅድ

### ከፊት የመምራት መመሪያ እና የኮሌጅና የሙያ ዝግጁነት

» 2022-2023 ከፊት የመምራት መመሪያ

» የኮሌጅና ሙያ ዝግጁነት

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# የሚጠበቁ ነገሮች፡- ሥርዓተ ትምህርት እና ማስተማር (ቀጣይ)



## የትምህርታዊ ምላሽ ዕቅድ

በወረርሽኙ ምክንያት ያልተጠናቀቁ ትምህርቶችን ለማጠናቀቅ MCPS የማስተማር እቅዱን መተግበሩ ይቀጥላል። የባለፈው አመት ግማሽ-አመት ትግበራ መረጃ በአጠቃላይ እድገት እና መሻሻልን ያሳያል፣ ነገር ግን በአንዳንድ አካባቢዎች እድገቱ ተመጣጣኝ አልነበረም። የታየበት ቀን፡-

- በክፍል ደረጃዎች 3፣ 6 እና 9 ውስጥ የማንበብ እና መፃፍ ደረጃ በአካል ተገኝቶ መማር ከተጀምረ በኋላ የአሳየው እድገት እና መሻሻል
- የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች እና አካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ጨምሮ በተለያዩ ክፍልፋይ-ቡድኖች ውስጥ የማንበብ እና መፃፍ መሻሻሎች ነበሩ
- በሂሳብ ላይ፣ በተለይም በክፍሎች 6 እና 9 ላይ የነበረው መሻሻል እኩል አልነበረም
- የ3ተኛ ክፍል ተማሪዎች በሂሳብ ላይ መሻሻል ያሳዩት መሰረታዊ ክፍል 3 የሂሳብ ይዘቶችን መማር ላይ ነው።
- ከሁሉም ትንሽ እድሜ ላይ የሚገኙ ተማሪዎቻችን በቅድመ ማንበብ እና መፃፍ ክህሎቶች ላይ አሻሽለዋል ግን አሁንም ክፍተቶች አሉ

የትምህርታዊ ምላሽ ዕቅዳችን አካል የሆነውን በክፍል ደረጃ መማር ላይ የቀጠለውን ትኩረት ለማሳካት፣ እያደረግን ያለነው፡-

» ሊተርሲ እና ሂሳብ ላይ በማተኮር

በወረርሽኙ ምክንያት በተማሪዎቻችን ላይ ያለው መሻሻል እንደዘገየ እናውቃለን እና በአለፈው የትምህርት ዘመን እድገት የታየ ቢሆንም፣ አሁንም ብዙ ተማሪዎች እና የተማሪ ቡድኖች ላይ ክፍተቶች አሉ። በዚህም የተነሳ፣ እድገታችንን ለማስቀጠል አሁንም ትኩረታችንን ያደረግነው ከፍተኛ ጥራት ያለው ማንበብና መፃፍ እና ሂሳብ ትምህርት ላይ ነው። በአንደኛ ደረጃ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ስነ ጥበብ (ELA)፣ MCPS የሊተርሲ ትምህርት መገንቢያ የሆኑትን ቁልፍ ክህሎቶች ለይቷል፥ ይህንን ተጨማሪ ጊዜ በመስጠት ለማስተማር መርሃ ግብሩን አስተካክሏል። አዳዲስ ግብዓቶች እና ሙያዊ እድገቶች ት/ቤቶቻችን ትንሹ እድሜ ክልል ላይ ለሚገኙ ተማሪዎቻችን የሚያስፈልገውን እውቀት እና መተግበሪያ መሳሪያ እያቀረቡልን ነው። በመላው ELA እና በሂሳብ፣ MCPS የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ፍላጎት ለማሟላት ከእንግሊዝኛ ቋንቋ እድገት ባለሙያዎች ጋር መስራትን ጨምሮ ሁሉንም ተማሪዎች መድረሳችንን ለማረጋገጥ ጥረታችን እያደገ ነው። በተጨማሪም ተማሪዎች ተቀባይነት እንዲሰማቸው እና በክፍላቸው ውስጥ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማበረታታት መምህራን በክፍል ውስጥ ጸረ-ዘረኝነትን እና ፀረ-አድሎአዊነትን የማስወገድ ስልቶችን እየተማሩ ነው።

» እንደ አስፈላጊነቱ በክፍል ደረጃ ማስተማር እና ያልተጠናቀቁ ትምህርቶችን ማጠናቀቅ

አዲስ መማርን ለመደገፍ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ መማሮችን መገምገማችንን እየቀጠልን ወደ ክፍል-ደረጃ ይዘት ቀጥለናል። የክፍል ደረጃ ትምህርት እየሰጠናቸው ወደፊት በመጓዝ ተማሪዎችን የበለጠ ወደ ኋላ እንዳይቀሩ መከላከል እንችላለን። አስተማሪዎችን እና የት/ቤት አመራሮችን ለመደገፍ፣ መሰረታዊ ሀሳቦች እና ክህሎቶች ላይ፣ ተገቢ የመማር ፍጥነት ላይ፣ የበለጠ ማወቅ ለሚፈልጉ የማጎልበቻ እድሎች መፍጠር ላይ፣ እና ተጨማሪ ክለሳ እና ትምህርት ለሚፈልጉ ተማሪዎች ድጋፍ መስጠት ላይ መመሪያዎችን አቅርበናል።

» የተማሪን ትምህርት መከታተል እና የማስተማር ስልትን ማስተካከል

ለኖሩ የሚችሉ የእውቀት ክፍተቶችን እየሞላን በክፍል ደረጃ ለማስተማር፣ አስተማሪዎች ተማሪዎቻቸው የሚያውቁትን እና ማድረግ የሚችሉትን መገንዘብ አለባቸው እና ይሄን መረጃ በመጠቀም የቀን ተቀን ትምህርታቸውን ያስተካክላሉ። ሁላችንም የተማሪን መማር ለመለካት በየጊዜው የመማር መገምገሚያን የምናውቅ ቢሆንም፣ ማለትም የምዕራፍ ፈተናዎች እና የትምህርት እድገት መለኪያዎች (MAP) ፈተና አይነት፣ አስተማሪዎች የመማርን መገምገሚያዎች መጠቀምን እንዲያሳድጉ ለማንበብና መፃፍ እንዲሁም ለሂሳብ መገምገሚያ ያሉትን መሳሪያዎች እንዲጠቀሙ MCPS ድጋፍ እያደረገ ነው። ይህ ማለት መምህራን ለተማሪዎቹ ካለፈው አመት ያልተጠናቀቁ ትምህርቶችን መቼ መጨረስ እንደሚፈልጉ እንዲያውቁ የተዘጋጁ ተግባራትን ይሰጧቸዋል፥ እናም የትኞቹ ተማሪዎች ለክፍል ደረጃ ፅንሰ-ሀሳቦች እና ክህሎቶች በመደበኛነት ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው ይለያሉ። ይህ ቀጣይነት ያለው ክትትል እና ማስተካከያ ሁሉም ተማሪዎቻችን በሊተርሲ እና በሂሳብ ከክፍል ደረጃ ወይም ከዛ በላይ እንዲሰሩ ትምህርቱ በተማሪ የመማር ፍላጎት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ያረጋግጣል።

# የሚጠበቁ ነገሮች፡- ሥርዓተ ትምህርት እና ማስተማር (ቀጣይ)



» ከትምህርት ቀን ውጭ ተጨማሪ ድጋፎችን መስጠት

የማጠናከሪያ ትምህርት እና ማስተካከያ ያልተጠናቀቁ ትምህርቶችን ለመጨረስ እና ተማሪዎችን በፍጥነት እንዲማሩ ለመርዳት የሚተገበሩ ናቸው። MCPS ከዚህ በፊት ያልተለመደ አይነት የማጠናከሪያ ትምህርት ለቤተሰቦቻቸው ምንም ወጪ ሳያስወጣ ለተማሪዎች መስጠቱን ቀጥሏል። ለበርካታ ተማሪዎች አሁን ባለው የክፍል ደረጃ ሥርዓተ ትምህርትን የሚደግፉ ከፍተኛ መጠን ያለው ትምህርት፣ አንድ ለአንድ እና በአነስተኛ ቡድን በሳምንት ብዙ ጊዜ በሊተርሲ እና በሂሳብ ትምህርት እየሰጠን ነው። የበለጠ የተጠናከረ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች፣ ከትምህርት ቤት በፊት፣ ወይም ከትምህርት በኋላ ጣልቃ ገብ ትምህርት እየሰጠን ነው። በተጨማሪም፣ "በፍላጎት ከተጠየቀ" የማጠናከሪያ ትምህርት፣ ወይም የቤት ስራ እርዳታ፣ ለማስተማር ከተፈቀደላቸው ኩባንያዎች ለማንኛውም ተማሪ 24/7 ትምህርት ይሰጣል።

» ሁሉም ትምህርት ቤቶችን የጋራ ትኩረት እና የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ

ሁሉም ትምህርት ቤቶች በማንበብና መፃፍ እና በሂሳብ ያልተጠናቀቁ ትምህርቶችን መጨረስ እና ለደህንነት እና ለት/ቤት የአየር ሁኔታ ቅድሚያ በመስጠት ተማሪዎች በዓመቱ መጨረሻ በማንበብና መፃፍ እና በሂሳብ ትምህርት በክፍል ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ መሆናቸውን በማረጋገጥ ይሠራሉ። ትምህርት ቤቶች ከትምህርት፣ የጨናማነት እና የአስተዳደር ዳይሬክተር እና ቡድኖቻቸው ጋር የትምህርት ቤት ማሻሻያ እቅዶችን ለማዘጋጀት፣ ስራቸውን ለመከታተል እና እነዚህን ግቦች ለማሳካት ለሰራተኞች ድጋፍ እና ትምህርት ለመስጠት ይሰራሉ።

» ሥርዓት አቀፍ ሥልጠና መስጠት

MCPS በማንበብና መፃፍ እና በሂሳብ ላይ ለአስተማሪዎች፣ ለት/ቤት አመራሮች እና ለማዕከላዊ ቢሮ አመራሮች ሙያዊ መማርን በተመለከተ ሦስት ቁልፍ መስኮችን ለይቶ አውጥቷል። የአንደኛ ደረጃ ማንበብና መፃፍን ለመደገፍ፣ ሙያዊ መማር ትኩረት ያደረገው መሰረታዊ ክህሎቶች ላይ ወደሚያተኩረው የማንበብና መፃፍ መዋቅራዊ ለውጥ ላይ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ላይ፣ ትኩረት የተደረገው በሁሉም የይዘት መስኮች ላይ ማንበብና መፃፍን ማዳበር ላይ ነው። በአንደኛ እና ሁለተኛ ደረጃዎች ላይ ሂሳብን የሚመለከት ሙያዊ መማር የሂሳብ ይዘቶችን በጥልቀት መረዳት ላይ ዕቅዳቸውን መሰረት ያደረጉ ምርጥ ተሞክሮዎችን ይመረምራል። የትምህርት ስርዓቱ መምህራን፣ የት/ቤት አመራሮች እና የዋና ጽ/ቤት ሰራተኞች ሁሉም ይህንን ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል። በዚህ ሥራ ምክንያት፣ MCPS K-12 ተማሪዎች በሊተርሲ እና በሂሳብ በክፍል ደረጃ ወይም ከዛ በላይ እንደሚሰሩ እንጠብቃለን፣ እና ሥርዓተ ትምህርት እና ትምህርቱ ከፍተኛ ጥራት ያለው እና በተማሪ የመማር ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ይሆናል።

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ማስጠናት እና ማስተካከያ ጣልቃ ገብነቶች



በትምህርት ክፍል፣ በዲስትሪክት እና በውጫዊ የፈተና መስፈርቶች በመጠቀም የክፍል ደረጃ ብቃታቸውን የማያሳዩ ተማሪዎች የማጠናከሪያ ትምህርት ወይም የጣልቃ ገብነት ድጋፍ ያገኛሉ። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) ስርአተ ትምህርት ለመጠቀም የሰለጠነ(ች) የ MCPS ሰራተኛ ወይም የውጭ አጋር ከት/ቤት ሠዓት በፊት፣ ከት/ቤት ሠዓት በኋላ ወይም በትምህርት ወቅት የማስተማር ስራ ይከናወናል።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) የማስተማሪያ ሞዴሎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

| ከፍተኛ መጠን ያለው ማስተማር እና ማስጠናት (TUTORING) | በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ጣልቃገብነቶች | በፍላጎት ጥያቄ ላይ የተመሠረተ ማስተማር፣ የቤት ስራ እገዛ |
|---|---|---|
| • ከዕለታዊ የክፍል ትምህርት ጋር በማጣጣም የክፍል-ደረጃ ሥርዓተ-ትምህርት ስኬትን በቀጥታ ይደግፋል<br>• "ትምህርት ማፋጠን"<br>• ከመደበኛ ትምህርት ውጭ፣ በአንድ ክፍል ጊዜ 60-90 ደቂቃዎች ያሉት በሳምንት ውስጥ ብዙ ክፍለ ጊዜዎች ይኖራሉ<br>• ቨርቹወል ወይም በአካል<br>• ተማሪዎች በፍላጎት ተለይተው ተጋብዘዋል<br>• በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ወይም በውጪ አቅራቢዎች ይሰጣል | የማንበብና መፃፍ መረጃ መሰረት ያደረጉ ማስተካከያዎች<br>• ኦርቶን-ጊሊንግሃም (Orton-Gillingham)<br>• በእርግጥ ጥሩ ንባብ ነው<br>• iዝግጁ ንባብ<br>• System 44<br>• ምንበብ 180<br>• iLit (እያደጉ የመጡ የብዝሀ-ቋንቋ ተማሪዎች<br>የሂሳብ መረጃ መሰረት ያደረጉ ማስተካከያዎች<br>• iReady ሂሳብ<br>• ሂሳብ 180 | • ለሁሉም ተማሪዎች፣ ለሁሉም የክፍል ደረጃዎች ክፍት ነው።<br>• ሁሉንም ኮርሶች እና የትምህርት ይዘቶችን መስጠት ይችላል።<br>• 24/7 እንደአመቺነቱ ተለዋዋጭ መርሐግብር ይኖራል።<br>• በአሁኑ ጊዜ ቨርቹወል<br>• በውጭ አቅራቢዎች ይሰጣል |

ከትምህርት ቀን ውጭ የክፍል ደረጃ ሥርዓተ ትምህርትን ለመደገፍ የሚከተሉት የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሊ.ተርሲ/ የሂሳብ ትምህርቶች በከፍተኛ ደረጃ ይሰጣሉ፥

የኤለመንተሪ ደረጃ ሂሳብ፡- ዩሬካ ሒሳብ (Eureka Math)—በተማሪዎች መካከል ጥልቅ የፈጠራ አስተሳሰብን የሚያበረታታ ጠንካራ ፕሮግራም ነው። ዩሬካ (Eureka) ተማሪዎችን በዘዴና በጥበብ ከቁጥሮች ጋር በጥልቀት እንዲሰሩ ጥረትና ቁርጠኝነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ ሲሆን፥ የሂሳብ ጽንሰ-ሐሳቦችን ከእውነተኛው ዓለም ጋር ማገናኘት፣ እና ፕሮብሌሞችን መፍታት ይማሩበታል።

የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ሂሳብ: ገላጭ የተብራራ ሒሳብ (Illustrative Math)—ተማሪዎችን በትብብር የሂሳብ ቋንቋ፣አካታች ትምህርታዊ ፈለጎችን እና የተመሰጠ አስተሳሰብ እና ምክንያታዊነትን በሚያበረታቱ ዲጂታል መሳሪያዎች ያሳትፋል።

የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሂሳብ: የተብራራ ሒሳብ (Illustrative Math) እና ሥርዓት ትምህርት 2.0 መስተጋብራዊ የመማር ተሞክሮን ለማዳበር ጥቅም ላይ ይውላሉ። የተማሪዎችን ወደ ልሳነ ክልኤ (ባለሁለት ቋንቋ) እንዲያመሩ የሚያደርግ፣ የስፓኒሽ እና የእንግሊዝኛ ትምህርትን የሚያጠናክርና ለማዳበር የሚረዳ ቀልጣፋ፣ የእድገት አካባቢ ለመፍጠር፣ መደበኛ የሆኑ ልኬት-ደረጃ/ ቤንችማርክ አደላንቴ (Benchmark Adelante) ልኬት-ደረጃ/ቤንችማርክ አድቫንስ ጋር እንዲጣጣም/እንዲጣመር ተደርጓል።

የኤለመንተሪ ELA፡ Benchmark Advance እና Benchmark Adelante—ከሜሪላንድ ኮሌጅ እና ለሙያ ዝግጁ የሆነ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነ ጥበብ (ELA) ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ ትምህርታዊ ግቦችን የሚደግፍ የተቀናጀ የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የመናገር እና የማዳመጥ ትምህርት ይሰጣል። ቤንችማርክ አደላንቴ (Benchmark Adelante) ተማሪዎችን ወደ ልሳነ ክልኤ (ባለሁለት ቋንቋ) እንዲያመሩ የሚያደርግ፣ የስፓንሽኛ እና የእንግሊዝኛ ትምህርትን የሚያጠናክርና ለማዳበር የሚረዳ ቀልጣፋ፣ ከቤንችማርክ አድቫንስ ጋር የሚጣጣም ትምህርት ነው።

ሁለተኛ ደረጃ ELA፡ StudySync—አጠቃላይ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነ ጥበብ ሥርዓተ-ትምህርት ዲጂታል ትምህርትን ከታለመለት ጽሑፍ ጋር በማጣመር ተማሪዎች መሳተፍ እና ውስብስብ ጽሑፎችን ለመተንተን መቻላቸውን ማረጋገጥ። StudySync ሁሉንም ተማሪዎች በንባብ፣ በመፃፍ፣ በመናገር/ በማዳመጥ እና በቋንቋ ከሜሪላንድ ኮሌጅ እና CareerReady ELA ደረጃዎች ለሚጠበቁ ነገሮች ያዘጋጃቸዋል።




Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# የማስጠናትና ማስረዳት ጣልቃገብነት (ቀጣይ)



### ጥቅም ላይ የዋሉ በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ጣልቃ ገብነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

| የማንበብና መፃፍ ማስተካከያዎች | የክፍል ደረጃዎች ተገልግለዋል |
|---|---|
| Orton Gillingham (OG):- የንግግር ድምፅ ግንዛቤ፣ ስነልሣን፣ የምልክት መልክትን ወደ ግልጽ ቋንቋ መተርጎም እና መረጃውን ወደ ምስጢራዊ ቋንቋ መቀየር ውስጥ ከፍተኛ ማሻሻል ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች እንደ ደረጃ III ንባብ ጣልቃ ገብነት ሊተገበሩ የሚችሉ ግልፅ፣ ስልታዊ እና ብዙ የስሜት ህዋሳት አጠቃቀም ዘዴዎችን ያስተምራል። | አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| በእርግጥ ጥሩ ንባብ (RGR) ነው፡ በድምፅ ግንዛቤ፣ በድምጸ ንግግር፣ ዲኮዲንግ እና ኢኮዲንግ ዘርፎች ጥልቅ ማሻሻል ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች ግልጽ፣ ስልታዊ እና ድምር የደረጃ III የንባብ ጣልቃገብነት ይሰጣል። ለተማሪዎች ሦስት RGR ጣልቃ ገብነቶች ይኖራሉ:- አቆጣጠር፣ በኃይል ድምፅ ማስጮህ እና HD ቃል። | አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ ደረጃ |
| iReady Reading:- የመረዳት ችሎታን ለማሻሻል ከፍተኛ ድጋፍ ለሚፈልጉ ተማሪዎች ግልፅ እና ስልታዊ የደረጃ III ጣልቃ ገብነትን ይሰጣል። | የአንደኛ ደረጃ |
| System 44:- መሠረታዊ የንባብ ችሎታዎችን ያዳብራል | መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| ንባብ/Read 180፡ አጠቃላይ ግንዛቤ እና ትርጉም ያለው የንባብ ችሎታ ማዳበር ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች መሰረታዊ የንባብ ክህሎቶችን ይሰጣል። | መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| iLit: በ 4ኛ፣ 5ኛ ክፍል፣ በመካከለኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚገኙ የ ESL ተማሪዎች ተጨማሪ የሊተርሲ ድጋፍ ይሰጣል | አንደኛ ደረጃ፣ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |
| **የሂሳብ ማስተካከያዎች** | **የክፍል ደረጃዎች ተገልግለዋል** |
| iReady Math:- የሂሳብ ትምህርት ማሻሻል ለሚፈልጉ ተማሪዎች ከፍተኛ ግልፅ እና ስልታዊ የደረጃ III ጣልቃ ገብነት ይሰጣል። | የአንደኛ ደረጃ |
| ሒሳብ/Math 180:- ለአልጀብራ 1 ለማዘጋጀት መሰረታዊ የሂሳብ ክህሎቶችን ይሰጣል | መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት |



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# የማስጠናትና ማስረዳት ጣልቃገብነት (ቀጣይ)

ሁሉም የማስጠናትና ማስረዳት ጣልቃገብነት የሚከተሉትን እርምጃዎች በመጠቀም ክትትል ይደረግባቸዋል።

| በከፍተኛ መጠን ማስጠናትና ማስረዳት | በማስረጃ ላይ የተመሰረቱ ጣልቃገብነቶች | ከፍተኛ መጠን ያለው አጋር / HIGH DOSAGE PARTNER እና በፍላጎት ላይ የሚደረግ የማስጠናት ትምህርት |
|---|---|---|
| የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች | የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች | ፈቃድ ያገኙ የውጪ አቅራቢዎች |
| • ክፍሎች<br>• MAP<br>• የዲስትሪክት ግምገማዎች<br>• የክፍል ጊዜ ማስታወሻ ፅሁፎች<br>• MCAP | • በጣልቃ ገብነት የሚመጣ እድገት<br>• MAP<br>• የዲስትሪክት ግምገማዎች<br>• የክፍል ጊዜ ማስታወሻ ፅሁፎች<br>• MCAP | • ክፍሎች<br>• MAP<br>• MCAP<br>• የክፍል ጊዜ ማስታወሻ ፅሁፎች |
| *መድረክ፡ የአፈጻጸም ጉዳዮች* | *መድረክ፡ በተለይ ለጣልቃገብነት + የአፈጻጸ ወሳኝነት* | *መድረክ፡ የአፈፃፀም ጉዳዮች እና የአቅራቢ መድረኮች* |
| **የመማር ማረጋገጫ** | | |

## የግምገማ ዕቅዶች

በተጨማሪም፣ ለግምገማ እና ለመረጃ ትንተና የተሰበሰበው የጣልቃ ገብነት መረጃ የእያንዳንዱን ተማሪ የግምገማ እቅድ በእያንዳንዱ የጣልቃ ገብነት/የማጠናከሪያ ሒደት መጨረሻ ላይ ለማሳወቅ ጥቅም ላይ ይውላል። የግምገማው ዕቅድ ለአስተማሪዎች እና ለወላጆች ይሰጣል። የልየታ መረጃ ከዕለታዊ የሂደት ሪፖርቶች ጋር በግምገማ እቅድ ውስጥ ይካተታል። በተጨማሪም፣ MCPS የተማሪዎችን የመማር ችግር ለመቅረፍ የተፈቀደውን የጣልቃ ገብነት መርሃ ግብሮች ተፅእኖ እና ቅልጥፍናን ለመገምገም፣ ከብዙ መለኪያዎች እና አጭር መረጃ ጋር የጣልቃ ገብነት መረጃን ይጠቀማል። የጣልቃ ገብ ጥረት ላይ መገኘትና አጠቃቀም ስኬትን ለመለካት ጥቅም ላይ ይውላል።

## የቅዳሜ ት/ቤት

የ MCPS ተማሪዎች ተጨማሪ የትምህርት ድጋፍን በቅዳሜ ትምህርት፣ በጆርጅ ቢ. ቶማስ የመማሪያ አካዳሚ (George B. Thomas Learning Academy) በሚሰጠው በኩል ማግኘት ይችላሉ።

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# የሚጠበቁ ነገሮች:
# ልዩ ትምህርት



የልዩ ትምህርት ቢሮ የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ደንብ (IDEA)፣ በሜሪላንድ ህግጋት (COMAR) እና MSDE መመሪያ መሰረት የቅድመ ጣልቃ ገብነት እና የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን መተግበሩን ይቀጥላል።

የቅድመ ጣልቃ ገብነት እና የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ከልደት እስከ 21 አመት እድሜ ላላቸው ተማሪዎች ይሰጣሉ። በግለሰብ ሁኔታ ላይ ተመርኩዞ የሚሰጥ የትምህርት መርሃ ግብር (IEPs) ላላቸው ተማሪዎች በልዩ ሁኔታ የተነደፈ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች በተማሪው(ዋ) IEP በተመዘገበው መሰረት ይሰጣሉ። ዲስትሪክቱ በፌዴራል እና በስቴት ደንቦች መሠረት የልዩ ትምህርት ግዴታዎችን የማሟላት አሠራሮችን አዘጋጅቷል። እነዚህ ግዴታዎች ከግምገማዎች ጋር የተያያዙ የጊዜ ሰሌዳዎችን እና ሰነዶችን፣ IEP ቡድን ስብሰባዎችን እና በልዩ ሁኔታ የተነደፉ መመሪያዎችን እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ያካትታሉ። ሁሉም ተማሪዎች IEP ወይም በግለሰብ የቤተሰብ አገልግሎት እቅድ (IFSP) ላይ በተገለፀው መሰረት ሙሉ አገልግሎት ያገኛሉ። ከመረጃዎች ግምገማ በኋላ በእነዚህ ሰነዶች ላይ ለውጦች አስፈላጊ ከሆኑ IEP ቡድኖች አገልግሎቶችን ለመተግበር እና/ወይም አስፈላጊ የሆኑትን IFSP/IEP ስብሰባዎች ለመጥራት ሁሉንም ህጋዊ ሂደቶች ይከተላሉ።

ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የሚያስፈልጉ የማስተማሪያ እና/ወይም አጋዥ ቴክኖሎጂዎች ይሰጣሉ። ለአጠቃላይ ትምህርት፣ ለልዩ ትምህርት እና ለእንግሊዘኛ ቋንቋ መዳበር (ELD) መምህራን፣ የአስተማሪ ረዳቶች፣ ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች እና አስተዳዳሪዎች የሙያ ማዳበር ትምህርት እና በሥራቸው ላይ ያተኮረ የማሰልጠኛ እድሎች ይሰጣሉ። እነዚህ እድሎች በልዩ ሁኔታ የተነደፉ መመሪያዎችን፣ ደረጃ III በማስረጃ ላይ የተመሰረተ የማንበብ፣ የመጻፍ እና የሂሳብ ጣልቃ ገብነት፣ የባህሪ እና ማህበራዊ ስሜታዊ ድጋፎችን እና ስልቶችን፣ እና የማስተማሪያ/የቴክኖሎጂ መርጃዎችን ይመለከታሉ።

## ህፃና ትና ትንንሽ ልጆች

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የህፃናት እና ታዳጊዎች ፕሮግራም (MCITP) በቤት ውስጥ ወይም በሌላ የተፈጥሮ አካባቢ በአካል ተገኝቶ አገልግሎት ይሰጣል። ወላጆች/አሳዳጊዎች ቨርቹወል አገልግሎቶችን ለማግኘት መምረጥ ይችላሉ።

## ቻይልድ ፋይንድ (Child Find)

ከ 3-5 አመት እድሜ ያላቸው ተማሪዎች ምልመላ እና ግምገማ በአካል በመገኘት ይከናወናሉ። በልዩ ሁኔታዎች ቨርቹወል ማጣሪያ ሊከናወን ይችላል። የማጣራት እና የግምገማ እርምጃዎች ሰፊ የወላጅ/አሳዳጊ ቃለ መጠይቅ፣ የቅድመ ትምህርት ቤት መምህር መጠይቅ፣ መደበኛ ያልሆኑ የእድገት እንቅስቃሴዎች እና ሌሎች ዶኩመንቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ። ደረጃቸውን የጠበቁ መለኪያዎች ማለት የወላጅ/አሳዳጊ ደረጃ መለኪያዎችን ጭምር የሚከናወኑ በተግባር እና/ወይም በአካል በመገኘት የእያንዳንዱ ግምገማ መመዘኛዎች እና የተማሪው(ዋ) ግላዊ ፍላጎቶች ናቸው። በቤታቸው ወይም ህጻን እንክብካቤ በሚደረግለ(ላ)ት አካባቢ የተማሪው(ዋ) ቀጥተኛ ምልከታ የሚካሄደው ሲያስፈልግ እና ሲቻል ነው። የግምገማ ውጤት IEP የመጀመሪያ ደረጃ የብቃት ማጣራት ስብሰባ አማካኝነት ለቤተሰቦች ይገለጻል። ልጁን/ልጅቱን ለመዋዕለ ሕፃናት ለማዘጋጀት የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን እንዲያገኝ ተገቢ ከሆነ IEP ተዘጋጅቷል።

K-12 እና/ወይም እስከ 21 ዓመት እድሜ ክልል ውስጥ ላሉ ተማሪዎች ማጣሪያ እና ግምገማዎች በአካል ይካሄዳሉ። የእያንዳንዱ ግምገማ መለኪያዎች እና የተማሪው(ዋ)ን ግላዊ ፍላጎቶች ግምት ውስጥ በማስገባት የወላጅ/አሳዳጊ ሚዛንን ጨምሮ ደረጃቸውን የጠበቁ መለኪያዎች በአካል ተገኝተው ይተገበራሉ።

# ልዩ ትምህርት (ቀጣይ.)

ባለሙያ ቴራፒስቶች፣ ፊዚካል ቴራፒስቶች፣ የንግግር/ቋንቋ ፓቶሎጂስቶች እና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎት ሰጪዎች አማካይነት የሚደረጉ ግምገማዎች በአካል ይካሄዳሉ። ግምገማዎች የወላጅ/አሳዳጊ ቃለመጠይቆችን፣ የተማሪ ምልከታዎችን እና እንደአግባቡ ደረጃቸውን የጠበቁ ሌሎች ተግባሮችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

## አገልግሎት መስጠት

MCPS እምብዛም መሰናክል በሌለብት ሁኔታ ለተማሪዎች አገልግሎት መስጠቱን ይቀጥላል። የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች እንዲማሩ እና የአካል ጉዳተኛ ካልሆኑ እኩዮቻቸው ጋር የትምህርት እድገት እንዲኖራቸው እና በትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ውስጥ እንዲሳተፉ በቀጣይ አጽንኦት በመስጠት ለሁሉም ተማሪዎች የሚሰጠውን የትምህርት እድሎችን ልዩነት እንዲያጠቡ የትምህርት ቤት ቡድኖች ይበረታታሉ።

## የማካካሻ/መልሶ ማግኛ አገልግሎቶች

ከዚህ ቀደም ለማካካሻ/የማገገሚያ አገልግሎቶች ብቁ ሆነው የተገኙ ተማሪዎች 2022 ሠመር መጨረሻ ላይ አገልግሎታቸው የማይጠናቀቅ ከሆነ 2022-2023 የትምህርት ዓመት ተለይተው የታወቁ አገልግሎቶቻቸውን ማግኘታቸውን ይቀጥላሉ።

## በድንገተኛ/አስቸኳይ ሁኔታዎች IEP መተግበር

ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች በልዩ ሁኔታ የተነደፈ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች በተማሪው(ዋ) IEP ውስጥ IEP የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች እቅድ ውስጥ በተመዘገቡ ውሳኔዎች መሠረት ተግባራዊ ይሆናሉ። MCPS ለትምህርት ቤት ቡድኖች MSDE የቴክኒክ ድጋፍ መግለጫ/ቡሌቲን ሰጥቷል፦ ልዩ ትምህርት - ቀጣይ የመማር እቅድ - በድንገተኛ ትምህርት ቤት መዘጋት ወቅት

የልዩ ትምህርት አገልግሎቶችን ቀጣይነት ማረጋገጥ አስፈላጊነት።

## የሰክሽን 504 እቅዶች (Section 504 Plans)

አንቀፅ 504 ዕቅዶች ያላቸው ሁሉም ተማሪዎች የመረጃዎቻቸውን ማመቻቻዎች ይደረግላቸዋል። የሴክሽን 504 ፕላን ኬዝ ማናጀር እንደአስፈላጊነቱ ወይም በወላጅ/በአሳዳጊ ጥያቄ በየትምህርት ዓመቱ ቢያንስ አንድ ጊዜ ቨርቹዋል ወይም በአካል የሰክሽን 504 እቅድ ስብሰባዎችን ያስተባብራል።

የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎትን በሚመለከት ጥያቄዎች ካሉዋችሁ፣ ከት/ቤት ርዕሰ መምህር እና/ወይም የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች ቢሮ ጋር በ240-740-3900 እባክዎን ይገናኙ።

# የሚጠበቁ ነገሮች፡- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቨርቹወል አካደሚ



ለ 2022-2023 የትምህርት ዓመት፣ MCPS ቨርቹወል ፕሮግራም ከአንደኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል ተማሪዎችን የሚያገለግል ይሆናል እ ና ፈቃድ ያገኘ የ MCPS የትምህርት ቀን መቁጠሪያን በመከተል፣ 180-ቀናት የሚከተል ጥምር የትምህርት ሞዴል ይጠቀማል። ድብልቅ የማስተማሪያ ሞዴል ሁለቱንም የተዋሃደ (ቀጥታ) እና ያልተዋሃደ (ለየብቻ-ገለልተኛ) ትምህርትን ያካትታል። ይህ ማለት ተማሪዎች በጥምር ትምህርት ተሞክሮዎች ይሳተፋሉ-አንዳንድ የመማሪያ ክፍለ ጊዜ በአንድ ጊዜ ከመላው ክፍል ጋር በመምህራን የሚመራ ሲሆን በአንዳንዶቹ የተናጠል ትምህርት ይሰጣል። የ MVA ተቀዳሚ/ዋና ትኩረቱ ሰራተኞች የተማሪዎቻቸውን ፍላጎቶች በሚያውቁበት እና እንደ ተማሪዎች በላቀ ሁኔታ ስኬታማ የሚሆኑበትን የትምህርት ቦታ/ሁኔታ የሁሉንም ተማሪዎች ግላዊ ፍላጎቶች የሚያሟላ ደህንነቱ የተጠበቀ፣ አካታች የኦንላይን ትምህርትን ማበልፀግ ነው። ፕሮግራሙ የሚከተሉትን ዋና ዋና ነገሮች ያካትታል፡-

- የተለመደ/መደበኛ የአጠቃላይ ትምህርት ኮርሶችን መስጠቶች
- የተፋጠነ እና የላቀ ትምህርት ኮርሶች
- ክለቦች እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ/ተጓዳኝ ተግባራት
- ተማሪዎች ሰፊ የመማር እድሎችን እና ልምዶችን የሚቀስሙበት ተሳትፎ፣ ድጋፍ፣ ጥራት ያለው ይዘት እና የቀጥታ ትምህርታዊ ተሞክሮዎች ይኖራሉ።

በተጨማሪም፣ ለሚሰሩ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች፣ ከትምህርት ቤት ውጪ ያሉ አማራጮችን ለሚፈልጉ እና በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት የማይገኙ የተፋጠነ እና የላቀ ኮርሶችን ለመማር ለሚፈልጉ MVA ልዩ እድልን ያቀርባል።

ተማሪዎች COMAR ደንቦችን የሚያከብር እና በኦንላይን የተዘጋጀ መመሪያን የሚደግፍ ልዩ bell መርሃ ግብር ይከተላሉ። የቀጥታ ትምህርቶች በየቀኑ ከሰኞ እስከ ዓርብ የሚካሄዱ ሲሆን፣ ኮርሶቹ በአካል ከሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ክፍለጊዜዎች ጋር በቅርበት ይጣጣማሉ። የተለያዩ የትምህርት ደረጃዎችን ለማስተናገድ የመነሻ እና የማብቂያ ጊዜዎችን በማስተካከል እንደ መደበኛ ትምህርት ቤት መርሃ ግብሮች ተመሳሳይ የሰዓቶች ብዛት ይኖራቸዋል። ተማሪዎች ከትምህርት ክፍሎቻቸው መምህራን በትምህርታዊ ፍላጎቶቻቸው ላይ ተጨማሪ ጊዜ እና ድጋፍ ለመስጠት የድጋፍ እና የመግቢያ ጊዜዎችን ለማካተት ዕለታዊ መርሃ ግብሩ በደረጃ ይስተካከላል። የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL) ሰዓቶች እንደ የተማሪ ሪኮርድ አካል ሆነው ይመዘገባሉ፥ እና የቨርቹወል አካዳሚው ተማሪዎች ይህንን መስፈርት የሚያሟሉበትን እድሎች ያካተተ ይሆናል።

በአካላዊ ወይም በስሜት ሁኔታዎች የተነሳ በተመደቡበት ት/ቤት ትምህርትን መከታተል የማይችሉ በመሆኑ ዲጂታል (digital) የትምህርት እድል ለሚፈልጉ ተማሪዎች፣ MCPS ጊዜያዊ ትምህርታዊ አገልግሎቶች አሉት።

በተጨማሪም MCPS ለመመረቂያ ፕሮግራሞች የኦንላይን መንገዶችን አቅርቧል፣ ይሄም መሟላት ያለበትን የመመረቂያ የኮርስ/ትምህርት ስራ ማግኘት ለማግኘት ለሚፈልጉ ተማሪዎች ነው።

በእነዚህ ፕሮግራሞች ላይ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ እባክዎን ይሄን ይጎብኙ፡-

- Interim Instructional Services
  ጊዜያዊ የማስተማሪያ አገልግሎቶች
- ኦንላይን መንገዶች/ Online Pathways



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ውጤት አያያዝ፣ በትምህርት መገኘት፣ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት



## ስለ ውጤት አያያዝ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በ 2022–2023 የትምህርት ዓመት "MCPS Regulation IKA-RA" የውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት አቀራረብ ወደ ተዘረዘሩት የቅድመ-ወረርሽኝ ደረጃ አሰጣጥ ፖሊሲዎችና ሂደቶች ይመለሳል። ሆኖም፣ በ 2020–2021 እና 2021–2022 የትምህርት ዓመታት ውስጥ በተማሮቻቸው ትምህርቶች ላይ በመመስረት፣ በወረርሽኙ ምክንያት የውጤት አሰጣጥ ሂደቶች ሲሻሻሉ፣ ትምህርት ቤቶች በእነዚያ ልምዶች ላይ ለመገንባት፣ ለተማሪ እና ለማህበረሰብ ፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት፣ተጨማሪ መመሪያ የሚሰጥ ሲሆን ይኼውም ለ 2022–2023 የትምህርት ዓመት ምርጥ ልምዶችን እና የሚጠበቁ ውጤቶችን ያንፀባርቃል።

ይህ የሚያካትተው፡-

- ተማሪዎችን ማስቀደም እና ሞገስ ያለው የውጤት አሰጣጥ። ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎች እንደገና ግምገማ እና እንደሁኔታው የማመቻቸት በርካታ እድሎችን ይሰጧቸዋል። MCPS ተማሪዎች በወረርሽኙ ወቅት ያጋጠሟቸውን እጅግ በጣም ከባድ ፈተናዎች ያስታውሳል እናም በማገገሚያ ወቅትም ይኼው ተግዳሮት ይቀጥላል።
- በእያንዳንዱ የማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ የሚመከሩ የተለያዩ በርካታ ስራዎችን መሥራት።
- በሁሉም ኮርሶች ወጥ የሆነ የውጤት ምዝገባዎችን (90% በሁሉም ተግባራት/ምዘናዎች፣ 10% ልምምድ/ዝግጅት) ማረጋገጥ።
- በዜሮ ከመመዝገባቸው በፊት የ "50% ደንብ" አጠቃቀምን እና የሚጠበቅባቸውን የሁለትዮሽ ግንኙነቶችን ማጉላት።
- ለአስፈላጊው የዲስትሪክት ምዘናዎች የሚፈለገውን 10% ምድብ በእንግሊዝኛ፣ እንግሊዝኛ ለሌሎች ቋንቋዎች ተናጋሪዎች (ESOL)፣ እና የሂሳብ ትምህርቶች በማስወገድ፣ ውጤት ባልተሰጣቸው gradebook ተርታ መተካት።

በተጨማሪም MCPS ከክሬዲት ማገገሚያ፣ትምህርት የመከታተል ጣልቃ ገብነት እና የውጤት ማሻሻያ ትግበራ ወደ ቅድመ ወረርሽኙ ወቅት ይመለሳል።

## ተጠያቂነት

### የ MCPS የትምህርት ማዕቀፍ ማረጋገጫ

የተማሪ ውጤት ሲገመገም፣MCPS የሚከተሉትን ጥያቄዎች መመለስ ይፈልጋል፡-

- ልጆች እየተማሩ ናቸው?
- በቂ ትምህርት/ዕውቀት እየቀሰሙ ናቸው?
- እንዴት እናውቃለን?
- ካልሆነስ፣ ለምን አልሆነም?
- ስለዚህ ምን ማድረግ ይኖርብናል?

የተማሪን ግስጋሴ ሙሉ ምስል ለማግኘት፣ ዲስትሪክቱ ተማሪዎች እንዴት እየሰሩ እንደሆነ ለመገምገም በርካታ መለኪያዎችን/መመዘኛዎችን ይጠቀማል። እነዚህ እርምጃዎች የተማሪን የትምህርት እድገት በሚገመግሙ የክፍል፣ የዲስትሪክት እና ውጫዊ አውዶች የሚከናወኑ ናቸው።

| | |
|---|---|
| የመማሪያ ክፍል ዳታ/መረጃ | ሪፖርት ካርድ |
| የዲስትሪክት ፈተና/ምዘና | የዲስትሪክቱ ግምገማዎች በቀጥታ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ከሥርዓተ ትምህርት ደረጃዎች ጋር የተጣጣሙ ናቸው |
| ውጫዊ ምዘና | የስቴት/ናሽናል ምዘናዎች |



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ውጤት አያያዝ፣ በት ምህርት መገኘት ፣ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት (ቀጣይ)



## መነሻ መስመር እና የተማሪ ውጤት ማስረጃ

2020-2021 የትምህርት ማዕቀፍ ማስረጃ ተማሪዎች ሊተርሲ እና ሂሳብ ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ለማወቅ እንደ መነሻ መስመር መረጃችን ሆኖ ያገለግላል። ይህ ማዕቀፍ የተለያዩ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነ ጥበብ እና የሂሳብ መመዘኛ/ግምገማዎች እያንዳንዳቸው ከሶስት ምድቦች በአንዱ የተመደቡ ናቸው፡ ክፍል፣ ዲስትሪክት፣ ወይም ውጫዊ። ከዚህ በታች የሚገኙት ለመጀመሪያ፣ መካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የመነሻ መረጃዎች ዝርዝር ሰንጠረዦች ከተማሪ ውጤቶች ጋር በዘር፣ በአገልግሎት ቡድን እና በፆታ ተከፋፍለው ነው።

### አንደኛ ደረጃ ት/ቤት

| | EOL ሊተርሲ ከመቶኛ | በ2025 የ90% ግብ ትንበያ | ከመቶኛ/ፐርሰንት የተሟሉ EOL ሂሳብ | በ2025 የ90% ግብ ትንበያ |
|---|---|---|---|---|
| ሴት | 59.2 | 66.9 | 59.0 | 66.8 |
| ወንድ | 53.4 | 62.6 | 59.5 | 67.1 |
| ኤዥያዊ | 77.6 | 80.7 | 83.4 | 85.1 |
| ጥቁር ወይ አፍሪካን አሜሪካን | 51.1 | 60.8 | 50.2 | 60.2 |
| ሂስፓኒክ/ላቲኖ | 33.4 | 47.6 | 37.0 | 50.3 |
| ነጭ | 76.4 | 79.8 | 80.8 | 83.1 |
| ሁሉም ሌሎች | 70.2 | 75.2 | 72.5 | 76.9 |
| ነጻ እና የቅናሽ ዋጋ የምግብ ስርዓት | 32.9 | 47.2 | 35.3 | 49.0 |
| ልዩ ትምህርት | 30.8 | 45.6 | 36.0 | 49.5 |
| ውስን የእንግሊዘኛ ችሎታ | 31.1 | 45.8 | 36.8 | 50.1 |



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ውጤት አያያዝ፣ በትምህርት መገኘት፣ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት (ቀጣይ)



## መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት

| | EOL ሊተርሲ ከመቶኛ | በ2025 የ90% ግብ ትንበያ | ከመቶኛ/ፐርሰንት የተሟሉ EOL ሂሳብ | በ2025 የ90% ግብ ትንበያ |
|---|---|---|---|---|
| ሴት | 73.6 | 77.7 | 60.0 | 67.5 |
| ወንድ | 66.5 | 72.4 | 55.8 | 64.4 |
| ኤሽያዊ | 87.4 | 88.1 | 84.8 | 86.1 |
| ጥቁር ወይ አፍሪካን አሜሪካን | 63.9 | 70.4 | 45.6 | 56.7 |
| ሂስፓኒክ/ላቲኖ | 50.5 | 60.4 | 34.5 | 48.4 |
| ነጭ | 88.0 | 88.5 | 80.0 | 82.5 |
| ሁሉም ሌሎች | 79.1 | 81.8 | 70.3 | 75.2 |
| ነጻ እና የቅናሽ ዋጋ የምግብ ስርዓት | 48.8 | 59.1 | 32.7 | 47.0 |
| ልዩ ትምህርት | 53.3 | 62.5 | 31.4 | 46.1 |
| ውስን የእንግሊዘኛ ችሎታ | 45.5 | 56.6 | 26.1 | 42.1 |

# ውጤት አያያዝ፣ በትምህርት መገኘት፣ ተሳትፎ እና ተጠያቂነት (ቀጣይ)



## ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

| | EOL ሊተርሲ ከመቶ | በ2025 የ90% ግብ ትንበያ | በመቶኛ/ፐርሰንት የተሟሉ EOL ሂሳብ | በ2025 የ90% ግብ ትንበያ |
|---|---|---|---|---|
| ሴት | 78.5 | 81.4 | 73.8 | 77.9 |
| ወንድ | 70.3 | 75.2 | 65.3 | 71.5 |
| ኤዥያዊ | 89.8 | 89.9 | 88.7 | 89.0 |
| ጥቁር ወይም አፍሪካን አሜሪካን | 69.6 | 74.7 | 62.2 | 69.2 |
| ሂስፓኒክ/ላቲኖ | 54.7 | 63.5 | 48.9 | 59.2 |
| ነጭ | 90.0 | 90.0 | 86.3 | 87.2 |
| ሁሉም ሌሎች | 83.0 | 84.8 | 76.7 | 80.0 |
| ነጻ እና የቅናሽ ዋጋ ምግብ ስርዓት | 55.1 | 63.8 | 48.8 | 59.1 |
| ልዩ ትምህርት | 57.8 | 65.9 | 47.0 | 57.8 |
| ውስን የእንግሊዘኛ ችሎታ | 38.3 | 51.2 | 36.2 | 49.7 |

ተማሪዎች አሁንም ማወቅ ሊያስፈልጓቸው የሚችሉ ትምህርቶችን ተፅዕኖ ለመገመት፣ የተለያዩ የመረጃ አያያዞች በተማሪ ቡድኖች፣ የመማሪያ ክፍል መረጃ (ማለትም ውጤቶች)፣ ከትምህርት ስርዓቱ ጋር የተጣጣመ በዲስትሪክት (district) ደረጃ የምዘናዎች መረጃ እና መደበኛ ግምገማዎችን ጨምሮ ምዘና ይደረግባቸዋል።

የአፈጻጸም ልዩነቶችን ለማወቅ መረጃው ከክፍል ደረጃ እኩዮች ውጤት እና ከብሔራዊ የውጤት መረጃ ጋር ይወዳደራል። የአካዳሚክ ግስጋሴ መመዘኛዎች (MAP) የንባብ እድገት እና የሒሳብ ፈተና ውጤቶች በዚህ አመት ከ 2022 ስፕሪንግ እና ፎል 2022 ውጤት ጋር ይነጻጸራል።

# ተጠያቂነት (የቀጠለ.)



## የ MCPS የትምህርት ማዕቀፍ ማስረጃ (ቀጣይ.)

የትምህርት ማዕቀፍ ማስረጃ የተማሪን ትምህርት ለመገምገም የሚያገለግሉ የተለያዩ የመማሪያ ክፍል፣ የዲስትሪክት እና የውጭ አካል የሚሰጣቸውን ምዘናዎች ያጠቃልላል። ማዕቀፉ የተማሪን ዝግጁነት እና ስኬት ተጠያቂነትን የሚለይ የብዙ መመዘኛ እርምጃዎችን አቀራረብ ይጠቀማል። የማዕቀፉ ዓላማ ተማሪ እየተማረ(ች) እንደሆነ ወይም ትምህርቱ እንዴት እንደገባቸው ማሳየት እንደሚችሉ የማወቅ መለኪያ ነው። የብዙ መመዘኛዎች አቀራረብ ተማሪዎች የተማሩትን እውቀት ለማሳየት እድሎችን ይጨምራል እናም ተማሪዎች የሚያውቁትን እና ማድረግ የሚችሉትን የበለጠ የተሟላ ምስል ይሰጣል። የመማር ውጤት ማስረጃን ለማያሳዩ ተማሪዎች የተማሪን ትምህርት እና ስኬታቸውን ለማሳደግ እንደ ትምህርት እና ጣልቃ ገብነት ያሉ ድጋፎችን ይሰጣሉ።

ተጨማሪ ድጋፎች የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለመለየት ጥቅም ላይ የሚውለው የትምህርት ማዕቀፍ ማስረጃ አንዱ ገጽታ NWEA የአካዳሚክ እድገት እርምጃዎች (MAP) የትምህርት እድገት ውጫዊ መመዘኛ ነው። የ NWEA MAP የአካደሚክ እድገት ምዘናዎች ከክፍል-ደረጃ እኩዮቻቸው ጋር ብቻ ሳይሆን ከብሔራዊ እኩዮቻቸው ጋር ማወዳደርንም ይጨምራል። ለፎል ውጫዊ ምዘና ለማካሄድ የ MAP እድገት፣ የሚከተሉት መለኪያዎች ከአንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ላሉ ተማሪዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ።

### ሰፕተምበር/ኦክቶበር 2021 የውጭ ግምገማ ይሰጣል

| ደረጃ | መሰረተ ትምህርት (ሊተርሲ) | ሂሳብ | የመለካት ዘዴ |
|---|---|---|---|
| ኤሌሜንታሪ ት/ቤት፦ ከመዋእለ ህጻናት እስከ 2ኛ ክፍል | MAP የማንበብ ቅልጥፍና | MAP-የመጀመሪያ ደረጃ | በ 50ኛ የናሽናል ፐርሰንት ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ አፈፃፀም |
| ኤሌሜንታሪ ት/ቤት፦ ከ3ኛ እስከ 5ኛ ክፍል | የ MAP እድገት - ንባብ | የ MAP እድገት - ሒሳብ | በ 50ኛ የናሽናል ፐርሰንት ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ አፈፃፀም |
| መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት (Middle School) | የ MAP እድገት - ንባብ | የ MAP እድገት - ሒሳብ | በ 50ኛ የናሽናል ፐርሰንት ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ አፈፃፀም |
| ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (High School) | የ MAP እድገት - ንባብ | የ MAP እድገት - ሒሳብ | በ 50ኛ የናሽናል ፐርሰንት ደረጃ ወይም ከዚያ በላይ አፈፃፀም |

* አፈፃፀም የሚለካው በ NWEA በተደነገገው መሠረት የክፍል-ደረጃ መስፈርቱን ለሚያሟሉ ወይም ከዚያ በላይ ውጤት ለሚያመጡ ተማሪዎች ነው።

# የተማሪው(ዋ) በክፍል ውስጥ ትምህርት መከታተል

## ትምህርት መከታተልን ሪፖርት ስለማድረግ

በየጠዋቱ ወላጆች እና/ወይም አሳዳጊዎች የልጆቻቸውን ጤንነት ማረጋገጥ አለባቸው። አንድ ልጅ የኮቪድ-19 ምልክት ለታየበት/ባት፣ ወላጆች እና/ወይም አሳዳጊዎች ልጃቸውን ቤት ማቆየት፣ ኮቪድ-19 ማስመርመር፣ እና የጤና አገልግሎት አቅራቢያቸው ጋር መገናኘትን ማሰብ አለባቸው። የምርመራ ውጤቶች ቫይረሱ እንዳለ ከአሳዩ የ MCPS ሪፖርት ማድረጊያ በመጠቀም ሪፖርት መደረግ አለባቸው። ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ ትምህርት ላይ የመገኘት ፖሊሲዎች እንደገና ይቋቋማሉ እና ይተገበራሉ። እባክዎን "MCPS Regulation JEA-RA" ያገናዝቡ፡- የተማሪ በትምህርት ላይ መገኘት/ክትትል። ይህም የእለት ተእለት ትምህርት ላይ መገኘትን፣ መዘግየትን፣ በፈቃድ መቅረቶችን እና ያለምክንያት መቅረትን፣ ሪኮርድ እና ሪፖርት ማድረግን ይጨምራል። ለአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ በእያንዳንዱ የትምህርት ቀን መጀመሪያ ላይ ተማሪዎች መገኘታቸው በየቀኑ ይመዘገባል። ለ 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣የተማሪዎች በትምህርት ላይ መገኘት በእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ እየተመዘገበ የእለት ተእለት የመገኘት ኮድ ጋር ይሰላል።

የተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ መገኘት በአስተማሪዎች እየተወሰደ Synergy የተማሪ መረጃ ቋት ውስጥ ይመዘገባል። ይህ መረጃ በወላጅ ፖርታል "ParentVUE" በኩል ለወላጆች ይተላለፋል። ተማሪ እንደሌለ ምልክት ሲደረግ፣ በአውቶሜትድ ጥሪ ተማሪው(ዋ) እንደሌለ(ች) ለወላጅ/አሳዳጊ ይገለጻል። ይህ በፍጥነት ጣልቃ ለመግባት እና አስፈላጊ ከሆነ በትኩረት ክትትል ለማድረግ ይጠቅማል። የእለት ተእለት በትምህርት ላይ የመገኘት ሪፖርቶች በአከባቢ ት/ቤት ደረጃ ይወሰዳሉ፥ ይህም የት/ቤት መሪዎች የተማሪዎችን በትምህርት ላይ የመገኘት ሁኔታ ለመገምገም እና በመደበኛነት ትምህርት ቤት ለመከታተል ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች ለመለየት ጠቃሚ ይሆናል። በመጀመሪያዎቹ ሶስት ሳምንታት የትምህርት ቤቶች ዋና ፅህፈት ቤት ሰራተኞች ወደ ትምህርት ቤት ያልተመለሱ ተማሪዎችን ለመለየት እና ለቤተሰቦች የማድረስ ሂደቶችን ለማቀድ በየቀኑ ይከታተላሉ። በት/ቤት እና በዲስትሪክት ደረጃ ያሉ በርካታ የተማሪ-ደረጃ እና አጠቃላይ ሪፖርቶች በትምህርት ላይ መገኘትን ለመከታተል እና እንደ አስፈላጊነቱ ፈጣን ጣልቃገብነት ለመውሰድ ያገለግላሉ።

በትምህርት ላይ መገኘትን ስለመቆጣጠር እንደገና የመጀመር መመሪያ ሰነድ በተማሪ እና ቤተሰብ ድጋፍና ተሳትፎ እና በልዩ ትምህርት ጽህፈት ቤት የተቀናጀ ሂደትን በማብራራት በተከታታይ ከትምህርት የሚቀሩ ተማሪዎችን ክትትል ለማድረግ እና የተለየ ጣልቃገብነትን/ማስተካከያዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ያግዛል።

## የጤናማነት/ድህንነት ቡድኖች

በ2022-2023 ትምህርት አመት ወቅት፣ ት/ቤት መከታተል እና መሳተፍ የሚቸገሩ ተማሪዎችን፣ ማህበራዊ-የስሜት ችግሮች ያጋጠማቸው ተማሪዎችን፣ እና የት/ቤት ስርዓት እና የማህበረሰብ ግብዓቶችን የሚፈልጉ ቤተሰቦችን ተደራሽ ለማድረግ ሁሉም ት/ቤቶች የተማሪ ደህንነት ቡድኖቻቸውን በመለወጥ አሻሽለዋል። የተማሪ ደህንነት ቡድኖች ቁልፍ አባላት የት/ቤት አስተዳደሮች፣ የት/ቤት ካውንስለሮች፣ የተማሪ ተወካይ ሰራተኞች (PPWs)፣ ማህበራዊ ሰራተኞች፣ የት/ቤት ስነ-ልቦና ባለሙያዎች፣ የወላጅ ማህበረሰብ አስተባባሪዎች (PCCs)፣ እና እያጀመረ ያለ ብዙ-ቋንቋ ተናጋሪነት ህክምናዊ ካውንስለሮች (ETCs) ናቸው። የተማሪ ደህንነት ቡድኖች መረጃዎችን ይተነትናሉ፣ የመነሻ ምክንያት ትንተናዎችን ያካሂዳሉ፣ እና አላማ የተደረጉ ማስተካከያዎችን ይተገብራሉ።

MCPS በጥምረት (Synergy) ባለብዙ-ደረጃዎች የድጋፍ ስርዓቶችን (MTSS) ፈጥሯል። የ MTSS መድረክ ለተማሪዎች የጣልቃ-ገብነቶች/ማስተካከያዎች በማህበራዊ-የስሜት ድጋፍ፣ በባህሪ ድጋፍ፣ እና ትምህርት ላይ የመገኘት ክፍሎችን በሚመለከት መተግበራቸውን ት/ቤቶች፣ እና ዲስትሪክቱ መቆጣጠር እና መመዘን እንዲችል ያደርጋል። የተማሪ ደህንነት ቡድን አባላት በሁሉም 210 ት/ቤቶች ውስጥ ለ MTSS መድረክ በ2022 ፎል ላይ ስልጠና ወስደዋል። ይሄ መድረክ በ2022-2023 ትምህርት አመት ሁለተኛ ሴሚስተር ላይ ቀለል ያለ አጀማመር ይኖረዋል። የሰመር የሙያ ትምህርት የሚካሄደው ከሙሉ MTSS መድረክ መጀመር አስቀድሞ ለ 2023-2024 ትምህርት አመት መጀመሪያ ነው።

## ቨርቹወል አካደሚ መከታተል/Virtual Academy Attendance

በቨርቹዋል አካዳሚ ላሉ ተማሪዎች በየእለቱ ተመሣሣይ ትምህርት ይሰጣል። ተማሪዎች በየቀኑ በክፍል መገኘት ይጠበቅባቸዋል። በ MCPS ፖሊሲ መሰረት እና በአካል ከሚሰጠው ትምህርት መመሪያ ጋር በተጣጣመ መልኩ ክፍል ውስጥ መገኘት በየቀኑ ይመዘገባል። የመጀመሪያ ደረጃ አስተማሪዎች በጠዋት አንድ ጊዜ ይመዘግባሉ፣የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መምህራን በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍለጊዜ መጀመሪያ ላይ ክፍል ውስጥ የተገኙትን/ያልተገኙትን እየተቆጣጠሩ ይመዘግባሉ። የሁለተኛ ደረጃ ክፍለ ጊዜ መገኘት በሲነርጂ/Synergy በተማሪ የመረጃ ቋት ውስጥ የተመዘገበውን የእለት ተእለት የክትትል ምዝገባ ለማስላት በአንድ ላይ ይጠራቀማል/ይከማቻል። ቨርቹዋል አካዳሚ አንደኛው በአንደኛ ደረጃ እና አንድ በሁለተኛ ደረጃ ሁለት የደህንነት/well-being ቡድኖች አሉት። እነዚህ ቡድኖች በየሳምንቱ እየተሰበሰቡ የሁሉንም ተማሪዎች የመገኘት እና የተሳትፎ መረጃ ይመረምራሉ። ተጨማሪ ትምህርት የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን በመለየት ተማሪዎችን ለመደገፍ ሂደቶችን እና እቅዶችን ያዘጋጃሉ። ሁሉም PPW በቨርቹዋል አካዳሚ ውስጥ ያሉትን ተማሪዎች ይደግፋሉ። ተማሪዎች አሁንም በአካባቢያቸው ትምህርት ቤት የተመዘገቡ በመሆናቸው፣ በቨርቹወል አካዳሚ ውስጥ ያሉ ካውንስለሮች በአካባቢ ትምህርት ቤት ከሚገኙ የካውንስል አገልግሎት አባላት ጋር የተቀናጀ ድጋፍ እና አገልግሎቶችን ይሰጣሉ።

# የተማሪዎች፣ የሠራተኞች እና የቤተሰብ ድጋፎች



MCPS ወረርሽኙ የተማሪዎችን፣ የሰራተኞችን እና የቤተሰቦችን የትምህርት፣ የማህበራዊ፣ እና የስሜት ጤናማነትን እንዴት እንደጎዳ ያውቃል። MCPS ተማሪዎች በአካል በመማር ከሚያቀዳጁት አወንታዊ ማህበራዊ እና ስሜታዊ ተሞክሮዎች ጋር ማገናኘቱን ይቀጥላል።

MCPS ተማሪዎችን፣ ቤተሰቦችን እና ወላጆችን በማህበረሰብ ተደራሽነት እሳቤ በማሳተፍ፣ ጎረቤቶችን እና የማህበረሰብ ቦታዎችን በመጎብኘት መረጃዎችን፣ ሪሶርሶችን እና የታለመ ድጋፍን ለቤተሰቦች ማድረስ ይቀጥላል። እንዲሁም ተማሪዎች፣ ወላጆች እና ቤተሰቦች ከትምህርት፣ ከማህበራዊ እና የጤና ሪሶርሶች ጋር የሚገናኙበትን መንገዶች ለማጉላት MCPS በማህበረሰቡ ውስጥ ዝግጅቶችን ለማቅረብ ከካውንቲ ኤጀንሲዎች ጋር በአጋርነት ይሠራል። MCPS ለእያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 1.0 ማህበራዊ ሰራተኛ ቀጥሯል እና ስራ አስጀምሯል። እነዚህ ማህበራዊ ሰራተኞች የተማሪ ደህንነት ቡድን ቁልፍ አካል ሆነው ያገለግላሉ። (የግንኙነት ዕቅዱን እዚህ ይመልከቱ)።

## ተማሪዎች

MCPS የተማሪዎችን፣ ቤተሰቦችን እና ሰራተኞችን አካላዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ-ልቦናዊ ፍላጎቶች በዲስትሪክት እና በት/ቤት ባሉት ፕሮግራሞች የመፍታት ጥረቱን ይቀጥላል። "Be Well 365" የማገገሚያ እቅድ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የማህበረሰቡን እና የሰራተኞችን ስጋቶች ለመፍታት ትምህርት ቤቶች መውሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች ይሰጣል። የማህበራዊ-ስሜታዊ (SEL) ትምህርቶች ከመዋዕለ ህጻናት እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ በተናጥል እና በተቀናጀ መልኩ ይከናወናሉ። MCPS ለተማሪዎች አዲስ SEL ሥርዓተ ትምህርት መስጠቱን ይቀጥላል። ሠራተኞች በአዲሱ የ SEL ሥርዓተ ትምህርት ላይ"—the Leader in Me" በእኔ ውስጥ ያለ መሪ የተሰኘ ሥልጠና አግኝተዋል። ከሪኩለሙ ስለ ትምህርት፥ ለእያንዳንዱ ተማሪ ስለ መሪነት፥ እያንዳንዱ ተማሪ ብቁነት እንዲኖረው/እንዲኖራት የማድረግ ባህልን ስለመፍጠር፥ እና የትምህርት ሲስተሞች በአካዳሚያ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማስቻል የትምህርት ባለሙያዎችን ሁለንተናዊ በሆኑ ውጤታማ ተሞክሮዎች እና መገልገያዎች ያነቃቃል/ያበረታታል። ትግበራው በሶስት ዓመታት ፈረቃ ይከናወናል። መተግበር የተጀመረው በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ነው።

## ሠራተኛ

MCPS ከ24,000 በላይ ለሆኑት ሰራተኞቹ አካላዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ-ልቦናዊ ጤናማነት በቁርጠኝነት ይሰራል። ጤናማ ሁኑ 365፣ ለሰራተኞች እና ለተማሪዎች፣ የኮቪድ-19 ተፅዕኖዎች ለመመርመር እና ለመቋቋም እየጣርን ለተማሪዎቻችንም በየቀኑ ድጋፍ በምናደርግበት ወቅት የሰራተኛ አባላቶቻችንን እና ቤተሰቦቻቸውን ለመደገፍ ጠቃሚ የሆኑ የዲስትሪክት (district) እና የማህበረሰብ ግብዓቶችን ለሰራተኞቻችን እናቀርባለን። የሰራተኞች ድጋፍ ፕሮግራም ያሉትን ሰራተኞች ጨምሯል እና አገልግሎቶችን፣ ግብዓቶችን እና ድጋፍ ለሰራተኞች እና ለቤተሰቦቻቸው ማቅረብ ቀጥሏል፣ ይሄንንም የሚያደርገው በካውንስሊንግ መርሀ ግብሮች፣ በማማከሮች፣ በቪድዮ መልዕክቶች፣ በጋዜጣዊ መልዕክቶች(newsletters) ፣ እና ጤናማነትን በሚያስተዋውቁ የተለያዩ ርዕሶች ላይ በሚሰጡ በጤናማነት አውደ ርዕዮች ነው። በተጨማሪም፣ ት/ቤቶች እና ቢሮዎች የሰራተኞችን ጤናማነት ከተማሪዎችም ጋር በጋራ ቅድሚ ይሰጣሉ፣ ለሰራተኞችም ተጨማሪ ግብዓቶች እና የጤናማነት ዝግጅቶች አሉ።

## ወላጆች እና ቤተሰቦች

MCPS ወላጆች/አሳዳጊዎች ልጃቸው (ልጆቻቸው) ስኬታማ እንዲሆኑ ለመርዳት የሚያስፈልጋቸውን ግብዓቶች፣ መሳሪያዎች እና መረጃዎችን መስጠቱን ይቀጥላል። የድጋፍ ሰራተኞች ምግብን፣ መኖሪያን፣ የአካል እና የአዕምሮ ጤናን ጨምሮ ከትምህርት ቤት ሲስተም እና ከማህበረሰብ ሪሶርሶች ጋር በማገናኘት ቤተሰቦችን ለመርዳት ዝግጁ ናቸው። ቤተሰቦች ለበለጠ መረጃ የት/ቤቱን ካውንስለር፣ የትምህርት ቤት ሳይኮሎጂስት፣ PPW፣ ESOL የሽግግር አማካሪ (ETC) ወይም PCC በትምህርት ቤታቸው ማግኘት ይችላሉ። ወላጆች ስለ ማህበራዊ-ስሜት ጤነኛ ቁመና፣ ስለ ርቀት ትምህርት ስትራቴጂዎች እና ድጋፎች፣ የወላጅና ልጅ መልካም ግንኙነቶች፣ ስለ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና ሌሎችም በርካታ አርዕስቶች ላይ የተዘጋጁ ስልጠናዎችን፣ አውደ ጥናቶችን እና የተቀዱ የቪድዮ ክፍለጊዜዎች ማግኘት ይችላሉ።

| ፓረንት አካደሚ/ PARENT ACADEMY | ስለ አእምሮ ጤንነት ተከታታይ WAYMAKING | ጥንቃቄ-የሚደረግባቸው ወቅቶች |
|---|---|---|
| www.montgomeryschoolsmd.org/departments/parentacademy/ | https://youtube.com/playlist?list=PLkZwAghwrSyvIgVRCWXjpiI4iBWRK0Lwl playlist?list=PLkZwAghwrSyvIgVRCWXjpiI4iBWRK0Lwl | www.youtube.com/playlist?list=PLkZwAghwrSytgi1re_2Sr8Dt8poZCHgP5 |

# የማህበረሰብ ተሳትፎ እና ግንኙነት



## የዲስትሪክት ስልታዊ ትግበራ ተነሳሽነት ቡድን

በዳግም መከፈት እና ማገገሚያ ሂደት ውስጥ ትርጉም ያለው እና ቀጣይነት ያለው የባለድርሻ አካላት ተሳትፎን ለማረጋገጥ፣ MCPS በ 2021-2022 የትምህርት ዓመት የዲስትሪክት ስትራቴጂክ ትግበራ ተነሳሽነት ቡድንን (DSIIT) አስጀምሯል እና ይህንን ስራ 2022-2023 የትምህርት ዓመት ይቀጥላል።

DSIIT አባላት፡ የወላጅ እና የማህበረሰብ ድርጅቶች ተወካዮችን፣ የሰራተኛ ማህበራት እና የት/ቤት እና የመስሪያ ቤት ሰራተኞች ተወካዮችን ያካትታሉ። አባላት በፕሮጀክት ቡድኖች ውስጥ በሰራተኞች እና በማህበረሰብ አማካሪዎች እየተመሩ ይሰራሉ፡ መልሶ መክፈት እና የማገገም ዕቅዶች ቁልፍ ቦታዎች ላይ ግብአት በመስጠት፣ በአፈፃፀሙ ላይ ግብረመልስ በመስጠት እና ስለወደፊት ተግባራት ለማቀድ በመደበኛነት ይገናኛሉ። የፕሮጀክት ቡድኖች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

» የትምህርት መሰናክሎችን ማቃለል

» በአብዛኛው በድህነት የተጎዱ ትምህርት ቤቶች ላይ ማተኮር

» ዲጂታል ትምህርት እና ድጋፍ

» የደህንነት/Well-Being ድጋፍ

» የኮቪድ-19 ስራዎች አማካሪ ቡድን

MCPS የኮሚዩኒኬሽን ጽ/ቤት የግንኙነት እና የስርጭት ውጤታማነትን የማዳበር፣ የማስተዳደር እና የመከታተል ሃላፊነት አለበት። ለዚህ ቢሮ ኃላፊነት ያለው ግለሰብ የኮሙኒኬሽን ዳይሬክተር ክሪስቶፈር ክራም (Christopher Cram) ነው።

ቢሮውን በሚከተሉት መንገዶች ማግኘት ይቻላል፡-

የዳይሬክተር ኢሜይል፡- christopher_c_cram@mcpsmd.org
የቢሮ ኢሜይል፡ pio@mcpsmd.org or AskMCPS@mcpsmd.org
የቢሮ ስልክ፡ 240-740-2837
AskMCPS phone 240-740-3000 | Spanish Hotline: 240-740-2845

# ቴክኖሎጂ

ትምህርት ቤቶች ለቴክኖሎጂ ተማሪ የአንድ ለአንድ ሞዴል ወይም ካርት ሞዴል ተግባራዊ ለማድረግ ምርጫ አላቸው። አብዛኛዎቹ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቻችን ተማሪዎች ክሮምቡክ (Chromebook) እና መያዣ ጋር የተመደቡበትን የአንድ ለአንድ ሞዴል ተቀብለዋል። በየቀኑ ከትምህርት ቤት ወደ ቤት ይዘውት እንዲመጡ ይጠበቃል። ይህ መገልገያ የማስተማር ስራዎችን ለማጠናቀቅ በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ ጥቅም ላይ ይውላል።

የካርት ሞዴል የክሮምቡክስ (Chromebooks) ስብስቦች በትምህርት ቀን ጥቅም ላይ እንዲውሉ በእያንዳንዱ የትምህርት ክፍል ውስጥ ይቀመጣሉ። አብዛኛዎቹ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቻችን ይህንን ሞዴል ተቀብለዋል። በቤት ውስጥ ክሮምቡክ (Chromebook) ማግኘት የሚያስፈልጋቸው በእነዚህ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች አንዱን አስመዝግበው ያለምንም ወጪ በትምህርት አመቱ ለአገልግሎት ቤታቸው መተው ይችላሉ። ሊጠገን የሚያስችል ብልሽት ካለው ወይም ከጠፋ ተማሪው(ዋ) እና ቤተሰቡ መሣሪያውን ስለመጠገን-ስለመተካት ከት/ቤታቸው ጋር ይነጋገራሉ። የጥገና/የመተካት ወጪው ሲከፈል ምትክ ወይም የተጠገነው መሳሪያ ይሰጣል። ስለ ጥገና/መተካት ፕሮግራም ዝርዝር ለቤተሰቦች እንዲሰራጭ ለትምህርት ቤቶች ይሰጣል።

በቤት ውስጥ የኢንተርኔት አገልግሎት የሌላቸው ተማሪዎች MCPS የሚሰጠውን Mifi መገናኛ ለቤት አገልግሎት መጠቀም ይችላሉ። የክሮምቡክስ (Chromebooks) እና Mi-Fi መገናኛ የልጆች የበይነመረብ አጠቃቀም ህግን የሚያከብሩ እና በማንኛውም ጊዜ ማጣሪያዎች እና መቆጣጠሪያዎች አሏቸው።

## በአካል

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለመጪው የትምህርት ዓመት ትምህርት ቤቶች ሙሉ በሙሉ በአካል ትምህርት እንደሚሰጥ ይጠበቃል። አስቸጋሪ ሁኔታ ያላቸው ተማሪዎች ለሞንትጎመሪ ቨርቹዋል አካዳሚ ማመልከት እና መከታተል አማራጭ ሲሆን እንዲሁም ለጊዜያዊ የማስተማሪያ አገልግሎት ማመልከት ይችላሉ። ሁሉም ተማሪዎች ለመማር ክሮምቡክስ (Chromebooks) እንደ ዋና መሳሪያቸው ይጠቀማሉ። MCPS Google አካውንት ለሁሉም ሰራተኞች እና ተማሪዎች ተሰጥተዋል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከኦንላይን ማመልከቻዎች እና ስርአተ ትምህርት በተጨማሪ፣ የኮርስ ቁሳቁሶችን፣ የቤት ስራዎችን፣ የውይይት መረቦችን፣ ጥያቄዎችን እና ሌሎችንም የሚያካትቱ የኦንላይን የኮርስ መስጫ ቋት ለመፍጠር ለመምህራን የካንቫስ ትምህርት አሰጣጥ ማኔጅመንት ሲስተም ይጠቀማል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመገናኛ አውታረመረብ ሁሉንም የተማሪ እና የሰራተኞች የትምህርት መሳሪያዎችን መደገፍ ይችላል፤የማስተማር ሒደት እና ምዘና እንከን የለሽ መሆን ስላለባቸው

## ቨርቹወል

ወደ ቨርቹወል ማስተማር መቀየር አስፈላጊ ከሆነ፣ ሁሉም ተማሪዎች በቤት ውስጥ የሚጠቀሙበት ክሮምቡክ (Chromebook) ያገኛሉ። Nearpod፣ PearDeck እና Zoom ኦንላይን የደንበኝነት ምዝገባዎችን ጨምሮ ተመሳሳይ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች ወደ ቨርቹወል መመሪያ መሸጋገሩን ለማረጋገጥ ጥቅም ላይ ይውላሉ። ካንቫስ እንደ ዋና የኮርስ ቋት ጥቅም ላይ ይውላል።

## ድንኳን

በአካል በማስተማር ወቅት፣ የካንቫስ መድረክን ለማስታዎቫዎች፣ የሚቀርቡ ትምህርቶችን፣ ቪዲዮዎችን፣ የቤት ሥራዎችን፣ የቀን መቁጠሪያዎችን፣ ጥያቄዎች እና ሌሎችንም ጨምሮ የኮርስ ቁሳቁሶችን ለመጫን አስተማሪዎች ሊጠቀሙበት ይችላሉ። መምህራን ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የማስተማሪያ ስራዎችን ለማዘጋጀት ብዙ የኦንላይን እና ቁሳዊ ሪሶርሶችን መጠቀም ስለሚችሉ እነዚህ ኮርሶች ሁሉንም የክፍል ስራዎችን ሊያካትቱ ወይም ላያካትቱ ይችላሉ። የካንቫስ መድረክ ከኮርስ ማህደር ወይም ማሰሪያ ጋር ተመሳሳይ ሲሆን መምህራን እና ተማሪዎች የሚያገኙት አንዱ የማስተማሪያ/የመማሪያ አገልግሎት መስጫ ነው።

የአጭር ጊዜ መቅረት ጉዳዮች ሲፈጠሩ የካንቫስ (Canvas) መተግበሪያ ግብዓቶች የተማሪን መማር ቀጣይነት ለመደገፍ ጥቅም ላይ ይውላሉ።

## የሠራተኛ ምደባ

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ትምህርት የሚያስተምሩ ሠራተኞችን ይለያል። በአንደኛ ደረጃ ደረጃ ት/ቤት፥ የንባብ ስፔሻሊስቶችን፣ የሰራተኞች ሙያ እድገት አስተማሪዎችን፣ የአስተማሪ ረዳቶችን፣ የክፍል አስተማሪዎችን፣ አስተዳዳሪዎችን እና ሌሎችንም ይጨምራል። በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፥ የትምህርት ይዘት አስተማሪዎች ያስተምራሉ።

ሁሉም ትምህርት ቤቶች ቀኑን ሙሉ መሸፈናቸውን ለማረጋገጥ ተዘዋዋሪ የሰራተኞች መርሃ ግብሮችን አዘጋጅተዋል። የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች ከበርካታ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን የሚደግፉበትን የክላስተር ሞዴል የመጠቀም አማራጭ አላቸው።

## ልዩ ትምህርት

ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ከሚሰጡት የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች በተጨማሪ ለልዩ ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች ዝቅተኛ እና/ወይም ከፍተኛ አጋዥ የቴክኖሎጂ መሳሪያዎች እና አገልግሎቶች በ IEP ቡድን ውሳኔ መሠረት ተሰጥተዋቸዋል።



Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
Expanding Opportunity and Unleashing Potential

# ከመደበኛ ትምህርት ውጪ የሚሰጡ እንቅስቃሴዎች እና አትሌቲክስ



## በት/ቤቶች መካከል የሚካሄድ አትሌቲክስ

ለኮቪድ-19 ጥንቃቄና ደህንነት ሲባል ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አሠራር ፕሮቶኮሎች እና የ MCPS የተማሪ-አትሌቲክስ የህክምና አማካሪ ኮሚቴ በሰጠው ሪኮመንዴሽን መሰረት MCPS የትምህርት ቤቶች አትሌቲክስ ፕሮግራም በአካል መስራቱን ይቀጥላል። ተማሪ-አትሌቶች፣ የሥራ ባልደረቦች፣ ተመልካቾች እና ሁሉም ባለድርሻ አካላት አሁን ያለውን Return to R.A.I.S.E. ስትራተጂካዊ እቅድ ላይ የተገለጹትን ሂደቶች እና ፕሮቶኮሎች መከተል ይጠበቅባቸዋል። ይህ እቅድ CDC፣ MSDE፣ የሜሪላንድ ፐብሊክ ስኩልስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አትሌቲክስ ማህበር እና በሞንትጎመሪ ካውንቲ ከተላለፉት መመሪያዎች ጋር ይጣጣማል። የኮቪድ-19 አትሌቲክስ መረጃ ድረ-ገጽ በፕሮግራም አፈጻፀሞች ላይ የቅርብ ጊዜ ማሻሻያዎችን የሚገልጽ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ ይሻሻላል።

## ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች እና ስነ- ጥበባት

MCPS ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ ተግባሮች እና የስነ ጥበብ ትምህርት ፕሮግራም በአካል ሥራውን ይቀጥላል። ተማሪዎች፣ ሰራተኞች እና እንግዶች የኮቪድ-19 ስርጭትን የመከላከል ስልቶችን እንዲከተሉ ይበረታታሉ።

MCPS የተማሪ ምስክር ወረቀት ለማግኘት በሚያደርጉት ተሣትፎ ተማሪዎች ክሬዲት ያገኛሉ።

# 2022-2023 የትምህርት ዓመት የቀን መቁጠሪያ

**2022-2023** Tradtional School Year Calendar¥ Montgomery County Public Schools

| | |
|---|---|
| **2022** | |
| July 4 | Independence Day—Schools and offices closed |
| August 22, 23, 24, 25, 26 | Professional days for teachers |
| August 29 | First day of school for students |
| September 5 | Labor Day—Schools and offices closed |
| September 14 | Early release day for students |
| September 26 | No school for students and teachers |
| September 30 | Early release day for students |
| October 5 | No school for students and teachers |
| October 24* | Professional day for teachers; no school for students |
| November 7* | Professional day for teachers; no school for students; end of quarter grading/planning |
| November 8 | Election Day—Schools and offices closed |
| November 21 and 22 | Early release days for students |
| November 23 | Systemwide Closure—Schools and offices closed |
| November 24 and 25 | Thanksgiving—Schools and offices closed |
| December 7 | Early release day for students |
| December 23, 27, 28, 29, 30 | Winter Break—No school for students and teachers |
| December 26 | Holiday—Schools and offices closed |
| **2023** | |
| January 2 | New Year's Day (observed)—Schools and offices closed |
| January 16 | Dr. Martin Luther King, Jr. Day—Schools and offices closed |
| January 27* | Professional day for teachers; no school for students; end of quarter grading/planning |
| February 20 | Presidents' Day—Schools and offices closed |
| March 3 | Early release day for students |
| March 15 | Early release day for students |
| March 31* | Professional day for teachers; no school for students; end of quarter grading/planning |
| April 3*, 4*, 5, 6 | Spring Break—No school for students and teachers |
| April 7 and 10 | Holidays—Schools and offices closed |
| April 21* | Professional day for teachers; no school for students |
| May 29 | Memorial Day—Schools and offices closed |
| June 16 | Last day of school for students; early release day |
| June 19 | Systemwide Closure—Schools and offices closed |
| June 20* | Professional day for teachers; end of quarter grading/planning |

* If the school year is disrupted by emergencies and schools are closed three or more days, dates identified as possible make-up instructional days include: October 24 and November 7, 2022; January 27, March 31, April 3, April 4, April 21, and June 20–23, 2023.

¥ This list of dates does not apply to Arcola and Roscoe R. Nix elementary schools, which will follow the 2022-2023 Innovative School Year Calendar.

Adopted: 1/13/22

Maryland's Largest School District
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

# 2022-2023 የትምህርት ዓመት የቀን መቁጠሪያ/ካላንደር

**2022-2023** Innovative School Year Calendar[¥] Montgomery County Public Schools

| **2022** | |
|---|---|
| July 4 | Independence Day—Schools and offices closed |
| July 6 | First day of school for students |
| July 29 | Early release day for students |
| August 12 | Early release day for students |
| August 15–19 and 22–26 | No school for students and teachers |
| September 2 | Early release day for students |
| September 5 | Labor Day—Schools and offices closed |
| September 14 | Early release day for students |
| September 26 | No school for students and teachers |
| September 30 | Early release day for students |
| October 5 | No school for students and teachers |
| October 6 and 7 | Early release days for students |
| October 24* | Professional day for teachers; no school for students |
| November 4 | Early release day for students |
| November 7* | Professional day for teachers; no school for students; end of quarter grading/planning |
| November 8 | Election Day—Schools and offices closed |
| November 21 and 22 | Early release days for students |
| November 23 | Systemwide Closure—Schools and offices closed |
| November 24 and 25 | Thanksgiving—Schools and offices closed |
| December 7 | Early release day for students |
| December 22 | Early release day for students |
| December 23, 27, 28, 29, 30 | Winter Break—No school for students and teachers |
| December 26 | Holiday—Schools and offices closed |
| **2023** | |
| January 2 | New Year's Day (observed)—Schools and offices closed |
| January 16 | Dr. Martin Luther King, Jr. Day—Schools and offices closed |
| January 26 | Early release day for students |
| January 27* | Professional day for teachers; no school for students, end of quarter grading/planning |
| February 17 | Early release day for students |
| February 20 | Presidents' Day—Schools and offices closed |
| March 3 | Early release day for students |
| March 15 | Early release day for students |
| March 30 | Early release day for students |
| March 31* | Professional day for teachers; no school for students; end of quarter grading/planning |
| April 3*, 4*, 5, 6 | Spring Break—No school for students and teachers |
| April 7 and 10 | Holidays—Schools and offices closed |
| April 21* | Professional day for teachers; no school for students |
| May 26 | Early release day for students |
| May 29 | Memorial Day—Schools and offices closed |
| June 15 | Early release day for students |
| June 16 | Last day of school for students; early release day |
| June 19 | Systemwide Closure—Schools and offices closed |
| June 20* | Professional day for teachers; end of quarter grading/planning |

* If the school year is disrupted by emergencies and schools are closed three or more days, dates identified as possible make-up instructional days include: October 24 and November 7, 2022; January 27, March 31, April 3, April 4, April 21, and June 20–22, 2023.

¥ This list of dates applies only to Arcola and Roscoe R. Nix elementary schools.

Adopted: 01/13/22

Maryland's Largest School District
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*



# ግብረመልሱን ያቅርቡ/ Submit Feedback

SCAN ME

የእርስዎ አስተያየት እና ግብረመልስ አስፈላጊ ከመሆኑም በላይ ለምናዘጋጀው እቅድ አስፈላጊ መረጃ ይሰጠናል። እባክዎ ይህንን ድህረ-ገፅ ይጎብኙ www.mcpssubmitfeedback.org ት/ቤቶችን እንደገና ስለመክፈት እቅዳችን ዓመቱን በሙሉ አስተያየት/ግብረመልስ ለመስጠት።

እባክዎን በሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከሎች (CDC) ይሄ ዕቅድ ማሻሻያ እንደሚደረግበት ይገንዘቡ።